# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 144 ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## “በአነስተኛ ግድቦች የመስኖ ልማትን ማጠናከርና የኤሌክትሪክ ኃይል አማራጭን የማስፋት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር)



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአነስተኛ ግድቦች የመስኖ ልማትን ማጠናከርና የኤሌክትሪክ ኃይል አማራጭን የማስፋት ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አሳሰቡ።

የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት አፈጻጸም ግምገማ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት በሐላላ ኬላ ተካሂዷል።

በግምገማው በዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ አመላካቾች የተመዘገቡት ውጤቶች ለኢትዮጵያ ቀጣይነት ያለው እድገት ትልቅ ተስፋ የሰነቁ መሆናቸው ተመላክቷል።

በዚህም የመስኖ ልማትን ጨምሮ የኃይል ዘርፉ፣ የወጪ ንግድ እንዲሁም በማዕድንና ኢነርጂ ዘርፍ የተጀመሩ የልማት ሥራዎች የሚያበረታቱ መሆኑ ተገልጿል።

የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም እንደሚያመላክተው ዓመታዊ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት 7 ነጥብ 5 በመቶ እንደሚሆን ይጠበቃል።

በግምገማው የሥራ መመሪያና ቀጣይ አቅጣጫ ያስቀመጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ በሁሉም ዘርፍ የተጀመሩ አበረታች የልማት ክንውኖች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው ብለዋል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የስድስት ወራት አፈጻጸም አመርቂ ውጤት የታየበት መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቀጣይ በተለይም በአነስተኛ ግድቦች የመስኖ ልማትን ማጠናከርና የኤሌክትሪክ ኃይል አማራጭን ማስፋት ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

የዜጎችን የመጠጥ ውሃ ፍላጎት በሚፈለገው መጠን

“በአነስተኛ ግድቦች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ወይዘሮ አበባ በርሄ

## መንግሥት ለሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑ ተገለጸ

**እፀገነት አክሊሉ**

አዲስ አበባ፡- በፌዴራሉ መንግሥት በኩል ያለው የሰላም ቁርጠኝነት በጣም የሚደነቅና ለተግባራዊነቱም እየተወጣ ያለው ሚና ከፍ ያለ መሆኑን በቀድሞ የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር የትግራይ ብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ መሪ እና በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ጽህፈት ቤት ሃላፊ ወይዘሮ አበባ በርሄ ገለጹ።

ወይዘሮ አበባ በተለይም ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳሉት መንግሥት የሰላም ሰምምነቱ ከመፈረሙም በፊት ሕዝቡ በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስበት ከለጋሽ አካላት ጋር በመሆን የተለያዩ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን ሲያቀርብ ቆይቷል። ይህ ደግሞ ለሰላም የነበረውን ቁርጠኝነት ያሳያል ፤ አሁንም ስምምነቱ መሬት እንዲይዝ ለማድረግ

መንግሥት ለሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ዶክተር ጋርዳቸው ወርቁ

## የአገው ፈረሰኞች ፌስቲቫል ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክር ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የአገው ፈረሰኞች ፌስቲቫል ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክር እንደሆነ የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እና የአገው ፈረሰኞች ማህበር ዐብይ ኮሚቴ አባል የሆኑት ዶክተር ጋርዳቸው ወርቁ ገለጹ።

የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እና የአገው ፈረሰኞች ማህበር ዐብይ ኮሚቴ አባል ዶክተር ጋርዳቸው ወርቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ 83ኛው የአገው ፈረሰኞች ፌስቲቫል በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ እና በአዊ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ አዘጋጅነት በትናንትናው ዕለት ተከብሯል።

ፌስቲቫሉ ከፈረስ ግልቢያ በተጨማሪ የተለያዩ የአገው ብሄረሰብ መገለጫ የሆኑ ባህላዊ ጭፈራዎች፣ ኤግዚብሽንና ባዛሮች፣ የስዕል አውደ ርዕይ፣ የቁንጅና ውድድሮች የተካተቱበት እንዲሁም የዞኑ ነዋሪዎች ያላቸውን ባህል ያሳዩበት መሆኑን ዶ/ር ጋርዳቸው ገልጸዋል።

ይህም በአሉን ለመታደም የመጡ እንግዶች የዞኑን ባህል እና ቋንቋ እንዲያውቁት ትልቅ ሚና አለው። በዓሉ የአገው ብሄረሰብ አባላት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያውያን ነው ያሉት ዶክተር ጋርዳቸው ኢትዮጵያውያን እርስበርሳቸው እንዲተዋወቁና ማህበራዊ

የአገው ፈረሰኞች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል
















ሙስናና ሌብነትን ለአገር ስጋት የማይሆኑበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ጠንካራ የምርምር ስራዎች ያስፈልጋሉ

ገጽ 4

ዜና

# ሐይቆችን ከብክለት ለመታደግ እየተሠራ ነው

**በሪሁ አረጋ**

አዲስ አበባ፡- ሐይቆችን ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ከሚደርስ ብክለትና ጥፋት ለመታደግ እየተሠራ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የኢኮሃይድሮሎጂና የውሃ ጥራት ዴስክ ኃላፊ አቶ ሰለሞን ዘሪሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ሐይቆች ከተለመደው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥርዓት ውጪ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ከብክለትና ከጥፋት እንዲሁም ከክረምት ወቅት ደለል ለመከላከል እየተሠራ ነው።

እንደ አገር እየተሠሩ ካሉት ሥራዎች በሎጎ ሐይቅ ዙሪያ የውሃ ዳርቻ ልማት ተጀምሯል ያሉት አቶ ሰለሞን፣ የጣና ሐይቅ ዳርቻ ለማልማትም ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ጥናት እየተካሄደ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በሐይቆች ዙሪያ ደኖችን በመትከል የተፈጥሮ ሂደትን በመጠበቅ ተፈጥሮ ራሷን በራሷ ከጥፋት እንድትከላከል በማድረግ የውሃ አካላትን ከጥፋት ለመታደግ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ እንደሆነም አቶ ሰለሞን ገልፀዋል።

በተፈጥሮ ሥነ ሕይወትና ሥነውሃ መስተጋብር ያላቸው በመሆኑ ሕይወት ያላቸው ነገሮችና ውሃ ተለያይተው መኖር የማይችሉ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በዙሪያቸው ደኖችን በመትከል ተፈጥሯዊ ሂደቱን በመጠበቅ ተፈጥሮ በራሷ እራሷን ከጥፋት እንድትከላከል ማድረግ ይገባል ሲሉ ገልፀዋል።

ሐይቆችን በክረምት ወቅት ከሚደርስባቸው ደለልና ብክለት ለመጠበቅ ከተለመደው አሠራር ውጪ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥርዓትን በመከተል ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ ሂደትን ጠብቆ ማስቀጠል ይገባል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ተፈጥሮ ሲጠበቅም በሥነ-ሕይወትና በሥነ-ውሃ ሕይወት መካከል ያለው ጠንካራ መስተጋብር ቀጣይነት ይኖረዋል ብለዋል።



**ሎጎ ሐይቅ**

ደኖች የውሃ መጠን፣ ጥራትና ብክለት ለማስተካከል ድርሻቸው ከፍ ያለ መሆኑን የተናገሩት አቶ ሰለሞን፣ ወንዞች መጠናቸውንና ፍሰታቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ በቋሚነት መሥራት ያስፈልጋል። ይህን ጠንካራ ተፈጥሯዊ መስተጋብር ዘለቄታውን እንዲጠብቅም እየተሠራ ነው ብለዋል።

በሐይቆች ዙሪያ የእርሻ፣ የከተሞች ኢንዱስትሪ ልማትና የተለያዩ ሰው ሰራሽ ተግባራት መስፋፋት ሐይቆች በደለል እንዲሞሉና በቀላሉ ብክለት እንዲደርስባቸው ያደርጋል፣ በመሆኑም የመከላከል ሥራውን ተፈጥሯዊ መንገዱን በማይለቅ መልኩ ማስፋፋት እንደሚገባ መክረዋል።

አቶ ሰለሞን አክለውም፣ ደኖች በክረምት ወቅት የዝናብ ጎርፍ ከተለያዩ ቦታዎች ተሸክሞ የሚያመጣቸውን ተንሳፋፊ ነገሮች፣ ንጥረ-ነገሮችና ውህዶች በማስቀረት ሐይቆች እንዳይበከሉ ከማድረግ ባሻገር፣ የሚመጣውን ደለልም በመያዝ ሐይቆች በእንቦጭ እንዳይወረሩ በመከላከል ረገድ ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ጠቁመዋል።

በተፈጥሮ ሂደት ላይ ያተኮረ ኢኮሃይድሮሎጂ የሚባል አዲስ ችግር ፈቺ ምርምር ተኮር የተቀናጀ ሳይንስ በመተግበርም ሐይቆችን ከጥፋትና ብክለት ለመታደግ በትኩረት እየሠሩ መሆኑን ገልጸዋል።

# በክልሉ እየጨመረ የመጣውን የማህፀን በር ካንሰር ለመከላከል እየተሠራ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ እየጨመረ የመጣውን የማህፀን በር ካንሰር ለመከላከል እየተሠራ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ ገለፀ።

የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር መንግሥቱ በቀለ በትናንትናው ዕለት በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ በኦሮሚያ ክልል የማህፀን በር ካንሰር ስርጭት እየጨመረ የመጣ ሲሆን የበሽታውን ስርጭት ለመግታት ቢሮው በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

ከዚህ በፊት እናቶች የማህፀን በር ካንሰር ምርመራ አድርገው ባለማወቃቸው ምን ያህል እናቶች ላይ በሽታው እንዳለ አይታወቅም ያሉት ዶክተር መንግሥቱ፤ አሁን ላይ የጤና ምርመራው በመስፋፋቱ በበሽታው የሚጠቁ ሴቶችን ቁጥር በግልፅ ማወቅ ተችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

ዶክተር መንግሥቱ እንደገለፁት፤ ከአንድ በላይ ሰው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም፣ የተለያዩ የአባላዘር በሽታዎች፣ የእድሜ መጨመር እና ኤችአይቪ በደማቸው ዉስጥ ያሉ ሴቶች ለበሽታረ የመጋለጥ እድላቸዉ ሰፊ ነው። የእነዚህ ምክንያቶች መኖር እና ይህን የሚመጥን ምርመራ አለመኖር የበሽታው ስርጭት እንዲጨምር አድርጓል።

ከክትባት አንፃርም ስንመለከት እድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ 14 ዓመት ያሉ ሴቶች ክትባቱን የሚወስዱት ቁጥር ከሁለት ሚሊዮን አላለፈም ያሉት ዶክተር መንግሥቱ፤ የማህፀን በር ካንሰርን ለመግታት የኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች 408 ከፍተኛና መካከለኛ የጤና ባለሙያዎችን በማሰልጠን የማህፀን በር ካንሰር ምርመራና ህክምና እየሰጠ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመሆን ወደ 396 የሚጠጉ የህክምና መሳሪያዎችን ወደ ጤና ተቋማት አስገብቶ ስራ ላይ ይገኛሉ ሲሉም አክለዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ የጅማ እና ሐረማያ ዩኒቨርሲቲዎች ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመሆን የካንሰር ህክምና ተቋም



**ዶክተር መንግሥቱ በቀለ**

አስመርቀው ወደ ስራ መግባታቸውን የገለፁት ኃላፊው፤ በተጨማሪም በቡራዩ እና ባሌሮቤ የካንሰር ህክምና ተቋም በክልሉ ወጪ እየተገነባ ይገኛል ሲሉ አስታውቀዋል።

በመሆኑም ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር መሻሻሎች መኖራቸውን ጠቁመው በዚህም የማሕፀን በር ካንሰር የምርመራ አቅም በ2011 ዓ.ም ከነበረው ጊዜ ጋር ሲነፃፀር 2014 ላይ በ 10 እጥፍ አድጓል ብለዋል።

በተጨማሪም ዶክተር መንግሥቱ በማህፀን በር ካንሰር ዙሪያ የሚሰጡ ግንዛቤዎችን በሰፊው ተደራሽ በማድረግ፤ የክትባት ስርጭትን በማስፋት እና ከዚህ ባለፈ አፋጣኝ ህክምና በማድረግ በሽታውን መግታት ይቻላል ሲሉ አስረድተዋል።

ምርመራውን ሲያደርጉ ከነበሩ ሴቶች መካከል በኦሮሚያ ከተማ ልማትና ቤቶች ልማት የሚሰሩት ወይዘሮ የሺህ ተመስገን፤ የማህፀን በር ካንሰር ምርመራ ለማድረግ አስቤ አላውቅም ብለው፤ የጤና ቢሮው ይህን ምርመራ ማዘጋጀቱ አስደሳች ነው ሲሉ ገልፀዋል።

በኦሮሚያ ገቢዎች የሚሰሩት ወይዘሮ ወርቅነሽ ታዬ በበኩላቸው፤ እኛ ሴቶች በራሳችን ምርመራ ለማድረግ ስለምንቸገር መንግሥት ይህን ምርመራ በማዘጋጀቱ ተመርምረን ውጤቱን አውቀን በጊዜ ህክምና እንድንወስድ ይረዳናል ሲሉ ተናግረዋል።



**አቶ ኤሊያስ ወልዱ**

# በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ እየተሠራ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች በአገር ውስጥ ተሰማርተው አገራቸውን እንዲጠቅሙ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን የኢትዮ- አሜሪካ ምክር ቤት ገለጸ። የአኅዋ እገዳ እንዲነሳ እየሰራ እንደሚገኝ ተጠቁሟል።

የኢትዮ- አሜሪካ ምክር ቤት በትናንትናው ዕለት ባለፉት ዓመታት አፈፃፀም እና የቀጣይ ዓመታት ትግበራ ላይ ያተኮረ ምክክር ሲያደርግ ሊቀመንበሩ አቶ ኤሊያስ ወልዱ፤ ምክር ቤቱ አስቻይ ሁኔታ እንዲፈጠርና የንግዱ ማሕበረሰብ እንዲጠናከር በትኩረት ይሰራል ብለዋል። በአገር ውስጥ ያሉ ተግዳሮቶችን በመቀነስ ባለሀብቶች ንግዳቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ የምክር ቤቱ መኖር ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለውም አመላክተዋል።

በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው ገብተው በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ እና በኢኮኖሚው እንዲሳተፉ ማድረግ የቀጣይ አምስት ዓመታት የትግበራው አካል መሆኑንም ነው የገለጹት።

የልዑካን ቡድኑ ለ10 ቀናት በሚኖረው ቆይታ ከመንግሥትና ከግሉ ዘርፍ አካላት ጋር ምክክር እንደሚያደርግም ነው የተናገሩት።

ባለፉት አምስት ዓመታት በኢትዮጵያ ቢሮ መክፈት፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም ጥምረት የመፍጠርና የስራ ትብብር የመሳሰሉ ስራዎች መተግበራቸውን አቶ ኤሊያስ አብራርተዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የኢኮኖሚ እድገት እንዲመዘገብ፣ ሰፊ የስራ እድል እንዲፈጠርና ተከታታይ የሥልጠና መርሃ ግብሮችን በማዘጋጀት በሰዎች ልማት በአቅም ግንባታ የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት አባላቱን ወክሎ ይሰራል።

ተሰሚነት የሚኖረው በጋራ በሚደረግ ትግል መሆኑን በማመን ጥምረቱ ተፈጥሯል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ የምክር ቤቱ አባላት ድጋፍ እንዲያገኙና መብታቸው እንዲጠበቅ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ይተጋልም ብለዋል።

በሌላ በኩልም፤ የአሜሪካ መንግሥት የአፍሪካ አገራት የተለያዩ ምርቶችን ወደ አሜሪካ ገበያ ከቀረጥና ከታሪፍ ነጻ በሆነ ሁኔታ በማስገባት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚያስችለው የንግድ ዕድል ኢትዮጵያን ማገድዋን አስታውሰዋል።

የኢትዮ- አሜሪካ ምክር ቤት ለአኅዋ ጥያቄ ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጠው ደብዳቤ በመጻፍ፣ የንግድ ማህበረሰቡን በመወከል ክትትል እየተደረገበት እንደሚገኝ ገልጸው፤ እገዳው የህብረተሰቡ ተጠቃሚነት ላይ የሚኖረውን ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ ተገንዝበው አዎንታዊ ምላሽ እንዲሰጠው እንደሚሰሩ አስረድተዋል።

አሜሪካ አኅዋን በፖለቲካ መሳሪያነት ተጽእኖ መፍጠሪያ የምታደርገው አካሄድ ትክክል አለመሆኑን ጠቅሰው፤ አኅዋ ለማሕበረሰብ ጠቀሜታው ጉልህ መሆኑን በመገንዘብ ክልከላው እንዲነሳ ጥያቄያችንን እንቀጥላለን ብለዋል።

ምክር ቤቱ ከአምስት ዓመታት በፊት በ35 አባላት የተቋቋመ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት የአባላቱ ቁጥር 400 በላይ ደርሷል።



አቶ ሺመክት ማሩ

## የእንስሳት ልማት ዘርፍን ለማሳደግ በዘርፉ የተመረቁ ባለሙያዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሰራ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የእንስሳት ልማት ዘርፍን ለማሳደግ በዘርፉ የተመረቁ ባለሙያዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሰራ መሆኑን የኢትዮጵያ ህብረት ስራ ኮሚሽን አስታወቀ።

በእንስሳት ልማት ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን ከመደበኛው አርብቶ አደር በተጨማሪ በዘርፉ ክህሎት ያላቸው ዜጎችን ማሳተፍ አስፈላጊ መሆኑ ተገልጿል።

ኢፕድ ያነጋገራቸው በኢትዮጵያ ህብረት ስራ ኮሚሽን የፕሮግራም አማካሪ አቶ ሺመክት ማሩ በእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ የተመረቁ በርካታ ዜጎች ቢኖሩም በዘርፉ እየተሰማሩ አለመሆኑን ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ በዘርፉ ያለውን ችግር ለመፍታት የሙከራ ፕሮጀክት ቀርጾ እየሰራ ነው ያሉት አቶ ሺመክት፣ መነሻውም አገር ውስጥ ያለው የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርት ጋር በተያያዘ ያሉ ችግሮችን መፍታት ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የወተት ፣ የእንቁላልና የስጋ ፍጆታ እጅግ አነስተኛ መሆኑን የገለጹት አቶ ሺመክት በእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ ሙያ ያላቸው ዜጎችን በማሰባሰብ ችግሩን ለማቃለል እየተሰራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ሺመክት ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በእንስሳት ተዋጽኦ ዘርፍ ዋጋ መወደድ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የምርት እጥረትም አለ። የተመቻቸ የአየር ንብረትንና የተማረ የሰው ሃይልን በመጠቀም ይህንን ችግር በመፍታት ከውጭ የሚገባን የእንስሳት ተዋጽኦ ማስቀረት ይጠበቅብናል።

ስለዚህም ማህበሩ በሙከራ ፕሮጀክቱ 100 ማህበራትን በማደራጀት በ 11 ዱም ክልሎች በሚገኙ 43 ከተሞች ላይ ስራ እንዲጀምሩ ለማስቻል እየተሰራ ነው ብለዋል።

እያንዳንዱ ማህበር 15 እና ከዚያ በላይ ሰዎችን የሚያቅፍ ሲሆን አሁን ላይ 20 ማህበራት ተደራጅተው ስራ ለመጀመር እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

አቶ ሺመክት ዘርፉን የሚደግፍ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ አለመኖር፣ የግንዛቤ ችግርና የሚደራጁ ሰዎች ቁርጠኛ አለመሆን ዘርፉ እንዳያድግ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ዋነኞቹ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የህብረት ስራ ማህበራት ሕዝቡን በመደገፍ በኩል የሚያበረክቱት ሚና ትልቅ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ከ 90ሺ በላይ ህብረት ማህበራት ፣ 400 አካባቢ ዩኒየኖች እንዲሁም 5 ክልላዊ ፌደሬሽኖች ይገኛሉ ብለዋል።

እነዚህ ማህበራት በጋራ ወደ 27 ሚሊዮን የሚሆኑ አባላቶችን የሚይዙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 60 በመቶ የሚሆኑት አባላት በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ መሆናቸውን አቶ ሺመክት ገልጸዋል።

አቶ ሺመክት አያይዘውም ኮሚሽኑ በከተማ አካባቢዎች የሚስተዋለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት አምራችና ሸማቹን በቀጥታ የማገናኘት ስራ እየሰራ ነው ብለዋል።

ለዚህም አንደ የእሁድ ገበያ የመሳሰሉ አምራችና ሸማቹን የሚገናኙ ትስስሮችን እየፈጠረ ሲሆን ለወደፊትም ቀጥታ አምራቹ ትላልቅ የህብረት ስራ ማእከላትን በማቋቋም ቀጥታ ከሸማቹ ጋር ትስስር እንዲፈጠር በማስቻል የምግብ ዋጋ መናርን ለመቆጣጠር የሚቻልበት መንገድ ላይ ይሰራል ብለዋል።

# በባቢሌ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ዝሆኖች ከፍተኛ አደጋ ተደቅኖባቸዋል

**ገመቹ ከድር**



አዲስ አበባ ፡- በሕገ ወጥ አደንና መሰል ምክንያቶች የዝሆኖች ቀጥር ተመናምኖ 310 ገደማ በደረሰበት የባቢሌ መጠለያ የሚገኙ ዝሆኖች ከፍተኛ አደጋ እነደተጋረጠባቸው ተገለጸ። ከዚህም የከፋ ጉዳት ሳይከሰትም በመጠለያው ውስጥ የሰፈሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በአስቸኳይ እንዲወጡም ተጠይቋል ።

የባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አደም መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት አራት ዝሆኖች በሕገወጥ አደን የተገደሉ ሲሆን ዝሆኖቹም አምስት ሰዎች ላይ ጉዳት አድርሰዋል።

የባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ዝሆኖችን ጭምሮ 31 አጥቢ እንስሳትንና ከ225 በላይ ዝርያ ያላቸውን አዕዋፍት የያዘ ሲሆን በኦሮሚያ እና በሶማሌ ክልሎች ወሰን መካከል ስለሚገኝ ሁለቱም ክልሎች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡ እንደሚገባ ኃላፊው አስታውቀዋል።

ኅብረተሰቡ በመሬት ወረራ መልክ ወደ መጠለያው በመግባት በዝሆኖቹ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ለመቅረፍ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ አደም፤ ሆኖም ግን መጠለያው ዉስጥ የሰፈሩትን የኅብረተሰብ ክፍሎች ማስለቀቅ ባለመቻሉ በዝሆኖች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ማስቆም እንዳልተቻለ ተናግረዋል። በዚህ ምክንያት የባለፈውን ዓመት ሳይጨምር በ2015 ዓ.ም ብቻ አራት ዝሆኖች በሕገ ወጥ አደን ተገድለዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ ፣ አሁን ላይ በመጠለያው ውስጥ የሚገኙ የዝሆኖች ቀጥር 310 ገደማ ሲሆኑ በሕገወጥ አደንና መሰል ምክንያቶች የዝሆኖቹ ቁጥር እየጨመረ አይደለም። የሚኖሩበት ደንም በሕገ ወጥ ሰፈራ እየተጨፈጨፈ በመምጣቱ ዝሆኖቹ የሚራቡበት ቦታ አጥተዋል ብለዋል።

በመጠለያው ውስጥ የሚገኙ የውሃ ምንጮች እየደረቁ በመሆናቸውና በመሰል ችግሮች የዝሆኖች ህልውና ብሎም ከመጠለያው የሚገኘው የቱሪዝም ገቢ ጥያቄ ውስጥ መግባቱን አቶ አደም ገልጸዋል።

ኃላፊው፣ ምርምርን መሰረት ያደረገ ዘላቂ መፍትሄ ለማስቀመጥ ጽህፈት ቤቱ ከሐረማያ ዩኒቨርሲቲ እና ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በመስራት ላይ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በተለይ የዝሆኖች ግድያ እንዲቆም የኦሮሚያ እና ሶማሌ ክልሎች አስፈላጊውን ትኩረት እንዲሰጡ ጠይቀዋል።

በባቢሌ ወረዳ አካባቢ የኢንቨስትመንት ፍላጎት እንዳለ ያወሱት አቶ አደም ፤ ኢንቨስትመንቱ ጠቃሚ ቢሆንም ለቱሪዝም ዘርፉ ቅድሚያ በመስጠት በመጠለያው ውስጥ ለሚገኙ እንስሳት እና አዕዋፍት እንክብካቤ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

መጠለያው ከቱሪዝም ሀብቱ በተጨማሪ የአከባቢውን አየር ጠባይ በማስተካከል ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘንብ በማድረግ አካባቢውን ከድርቅ ለመከላከል ጉልህ ሚና እንዳለውም አክለው ገልጸዋል።

በተለያዩ ምክንያቶች እና በሕገወጥ አደን 10 ዝሆኖች በባቢሌ መጠሊያ ውስጥ መገደላቸውና በአጸፋ እርምጃ 8 ሰዎች መቁሰላቸውን ኅዳር 29 2015 ዓ.ም ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት መዘገቡ ይታወሳል።

# “የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያፋጥኑ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል”

\- ቆስጠንጢኖስ በርሄተስፋ(ዶ/ር)

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- አሁን ላይ የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያፋጥኑ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርሄተስፋ አስታወቁ።

በተያዘው የፈንጆቹ ዓመት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስመልክቶ በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት እና በፕላን ኮሚሽን ትንበያ መሰረት በማድረግ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርሄተስፋን አነጋግሯል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንደገለጹት፣ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው ስምምነትና ያለው እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ተደምረው በቀጣይ የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን ትልቅ አቅም ይፈጥራል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው እንደሚሉት፤ በተለይም ከዓለም ባንክና ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅቶች ጋር ለመስራት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።

ኢትዮጵያ በእርዳታ ከዓለም ባንክ፣ ከዓለም አቀፍ የገንዘድ ድጋፍ እና ከቻይና እንዲሁም ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስታገኝ የነበረው 5 ቢሊዮን ዶላር ዲፕሎማሲዋን በማጠናከር እንደገና የማግኘት እድል መኖሩን ያስረዱት ምሁሩ፤ በአንዳንድ አካባቢዎች የተስተጓጎሉ የልማት ሥራዎች ወደ ሥራ እንደሚገቡና አቅም እንደሚፈጥሩ አስረድተዋል።



በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ከ74 ሚሊዮን ሄክታር በላይ የሚታረስ መሬት እና 122 ቢሊዮን ኪዩቢክ ውሃ ባለቤት አገር መሆኗ ሌላው የኢኮኖሚ አቅም ነው ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ በተለይም በግብርናው ዘርፍ የተጀመረው የበጋ መስኖ ስንዴ፣ ቡናና በሌሎች ዘርፍ የታየው አበረታች ውጤት በማጠናከር በውጭ ምንዛሪ ከውጭ የሚገቡትንና የዋጋ ንረቱን የሚያባብሱ እንደ ዘይትና ስኳር የመሳሰሉት ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ማምረት እንደሚቻልም ጠቁመዋል።

በአገሪቱ የተገነቡትና እየተገነቡ ያሉ እንደ ታላቁ ህዳሴ ግድብ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችና ኢንዱስትሪ ፓርኮች ተጠናቅቀው ወደ ሥራ ሲገቡ ለኢኮኖሚ እድገቱ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ያብራሩት ምሁሩ፤ አገሪቱ ካላት ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች በተጨማሪ ያላትን እምቅ የአምራች ሃይል ወደ ልማት ለማዞር ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ ገልጸዋል።

መንግሥት ከፖለቲካ ወገንተኝነት በጸዳ መልኩ አቅምና እውቀት ያላቸውን አመራሮች በልማት ዘርፍና በሌሎች ዘርፎች መመደብ መጀመሩ ሌላው የእድገት አቅም መሆኑን ያወሱት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ይህ እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትና በዋነኝነት እድገቱን የሚገታ የሙስና ሰንሰለት ከማስወገድ አኳያ ትልቅ የቤት ሥራ መስራት እንደሚጠበቅበት አመላክተዋል።

በቅርቡ በቀረበው የዋና ኦዲተር መረጃ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እንደሚባክን የገለጹት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ችግሩን ለመቅረፍ መንግሥት የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ግብረሃይል ማቋቋሙ የተሻለ ውጤት ለማመዝገብ ምቹ አጋጣሚ ቢሆንም ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ቅንጅታዊ አሰራርን በመዘርጋት የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን መስራት አስፈላጊ ነው ሲሉ መክረዋል።

# ሙስናና ሌብነትን ለአገር ስጋት የማይሆንበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ጠንካራ የምርምር ስራዎች ያስፈልጋሉ

## - የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮችን በተመለከተ ጥናቶችን እያካሄደ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ለአገርና ለዜጎች ደህንነት አደጋ የሆነውን ሙስናና ሌብነት ስጋት የማይሆንበት ደረጃ ላይ ለማድረስ በሳይንሳዊ ዘዴ የታገዘ የምርምር ስራና የነቃ የዜጎች ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ። ዩኒቨርሲቲው ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮችን በተመለከተ ጥናቶችን እያካሄደ ነው።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ አሰጣጥ ዙሪያ የሚታየውን የሙስና እና ድለላ ችግር በተመለከተ ባካሄዳቸው ጥናቶች ላይ ትናንት የምሁራንና የባለድርሻ አካላት ውይይት ተካሂዷል።

በውይይት መድረኩ መክፈቻ ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር ተመስገን ቡርቃ እንደገለጹት፣ ላለፉት ዓመታት አገራችንን ለማፍረስ ያልተሸረበ ሴራ አልነበረም። ዛሬም መልኩን እየቀየረም ቢሆን ዋጋ እያስከፈለ ነው። ይህን ግንባር የሚያንቀሳቅሱት ደግሞ በንቅዘት የተዘፈቁ በሕገ ወጥ መንገድ ሀብት የሚያጋብሱ ሕገ ወጥና ድርጊቱን የሚያመቻቹ ደላሎች ናቸው። ሙስና እና ሌብነት አገርንና ዜጎችን አደጋ ላይ የሚጥልና የሚጐዳ ትልቅ የንቅዘት በሽታ ነው። ለአገር ልማት፣ ለዴሞክራሲ እድገት እንቅፋት የሆነውን ንቅዘት በጥናት በማስደገፍ መከላከል ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው።

እንደ ዶክተር ተመስገን ገለጻ፤ ንቅዘት ጥቂቶች ባልሰሩበት የሚከብሩበት፣ የአገርን ልማት፣ እድገት፣ ዴሞክራሲ የሚያቀጭጭ የሕዝቦችን ኑሮ የሚያጎሳቁል ነው። ‹‹ዩኒቨርሲቲው የሚያካሂደው ምርምር አገራችን ያሉባትን ችግሮች ለመቅረፍ የሚረዳ ነው››። ጥናቶችን መሬት ላይ በማውረድ መንግሥት ለፖሊሲ ማሻሻያ ግብአት እንዲወስድ ማድረግ አስፈላጊ ነው።



ዶክተር አለማየሁ ደበበ



ዶክተር ተመስገን ቡርቃ



ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚካሄደው ምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት አገራችን ያሉባትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ሊሆኑ ይገባል ያሉት የቦርድ ሰብሳቢው፤ የንቅዘትና የሌብነት ተግባር በመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማት በመዛመቱ ዜጎች ፍትህን ጨምሮ በርካታ አገልግሎቶችን በገንዘብ እንዲገዙ እየተገደዱ ነው። ይህ አይነቱ ድርጊት የመንግሥትንና የሕዝብን ሀብት ከመዝረፍ አልፎ በሌብነት በተገኘው ገንዘብ አሻጥር በመፍጠር የአገርን ሰላም እስከማወክ እየደረሰ ነው ብለዋል።

በሙስና ተግባር ውስጥ የተዘፈቁ ብዙዎች አንዱን ወንጀላቸውን በሌላ ወንጀል ለመሸፈን የማይፈነቅሉት ድንጋይ፣ የማይጓዙት መንገድ እንደሌለ የገለጹት ዶክተር ተመስገን፤ ሌቦች ከፍትህ ተጠያቂነት ለማምለጥ ሲሉ በሚያደራጇቸውና የገንዘብ ድጋፍ በሚያደርጉላቸው ቡድችኖች የሕዝብን ሰላማዊ ኑሮ በማዋከ የመንግሥትን ሃሳብ ለመከፋፈል ሙሉ አቅማቸውን እየተጠቀሙ ነው ብለዋል።

ንቅዘት ከመንግሥትና ከሕዝብ የተሰበሰበ ገንዘብን ኃላፊነትንና አደራን ለግል ጥቅም የማዋል ተግባር ነው። ተግባሩ በየትኛውም የሥልጣን ተዋረድ ሊፈጸም የሚችል ነው። ይህ ተግባር የሕዝብና የአገር ደህንነት አደጋ ላይ እንዲወድቅ የሚያደርግ ነው። ንቅዘት የልማትን እንቅስቃሴ በማስተጓጎል ኢንቨስትመንትን በማቀንጨር፣ የመንግሥት አገልግሎትን በማጉደል፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዳይጎለበት የሚያደርግ እኩይ ተግባር መሆኑን የቦርድ ሰብሳቢው ገልጸዋል።

ዶክተር ተመስገን ሙስና የሕግ የበላይነትን የሚጻረር እኩይ ተግባር በመሆኑ ሁሉም ዜጋ በንቃት ሊታገለው ይገባል። ሙስና ከአገር ሰላም አልፎ በዜጎች ደህንነት ላይ አደጋ እስከ መደቀን ደርሷል። ይህንን አደጋ ለአገር ብሎም ለዜጎች ደህንነት አደጋ ከማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ በሳይንሳዊ የምርምር ስራዎች ማገዝ ያስፈልጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው ከተሞች በብቃት እንዲመሩ፣ ፍትህ እንዲረጋገጥ፣ ሙስናና ሌብነት እንዲቀንስ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው። የጥናቱ አገርንና ሕዝብን እየጎዳ ያለውን ሙስናና ሌብነት ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ በመለየት መንግስት በፖሊሲ የተደገፈ እርምጃ እንዲወስድ ግብዓት ለመስጠት ነው። ሙስናና ሌብነትን ማክሸፍ የሚቻለው በዜጎች ንቁ ተሳትፎ፣ በእውቀትና በጥበብ በታገዘ ጥናትና ምርምር ስራዎች በመደገፍ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር አለማየሁ ደበበ በአገልግሎት ዘርፍ፣ በትምህርት፣ በጤናና በመድሃኒት አቅርቦት፣ በኢንቨስትመንት፣ በግዥ አሰራር፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ዘርፍ እንዲሁም በድለላ ላይ ያተኩሩ ጥናቶች ቀርበው ትችት ተደርጎባቸው ተከልሰው ተግባራዊ እንዲሆኑ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ዶክተር አለማየሁ አያይዘውም፤ በእለቱ ለሚቀርቡት 21 ጥናቶች ከ117 ተቋማት መረጃ መሰብሰቡን ገልጸዋል።

በመድረኩ የክልል የጸረ ሙስና ቢሮ ኃላፊዎች፣ ምሁራን፣ ተመራማሪዎችና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# “በአነስተኛ ግድቦች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መመለስና የተሻለ ሥራ ማከናወንም የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫ መሆን እንዳለበት አመላክተዋል።

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በስድስት ወራት 48 ሺህ የውሃ ፓምፖችን በማስገባት ለመስኖ ሥራ የላቀ ሚና እንደነበረው አስታውሰው፤ ይህም ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል ሲሉ አስገንዝበዋል።

በቀጣይ የመስኖ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ከመደገፍ ባለፈ በየአካባቢው አነስተኛ የመስኖ ግድቦችን መሥራት ላይ ማተኮር ይገባልም ነው ያሉት።

በሕገ-ወጥ መልኩ የሚወጡ ማዕድናትን መቆጣጠርና ከውጭ የሚገቡ የግንባታ ግብዓቶች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ መሥራትም ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ መሆን አለበት ብለዋል።

እንደ ኢዜአ ዘገባ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ባለፉት ስድስት ወራት ለኢኮኖሚው ማደግ ትልቅ ሚና መወጣቱን አስታውሰው፤ በቀጣይ የዋጋ ግሽበትን በመቆጣጠር የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመፍጠር መሥራት አለበት ብለዋል።

የሕገ-ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን መቆጣጠር፤ በንግድ ሰንሰለቱ የሚስተዋሉ ዘርፈ-ብዙ ማነቆዎችን መፍታት ይገባልም ነው ያሉት።

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ለ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ወደ ፊትም ተጨማሪ ሥራዎች ያስፈልጋሉ ብለዋል።

# መንግሥት ለሰላም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እየሄደበት ያለው አካሄድ የሚበረታታ ነው።

እንደ ወይዘሮ አበባ ገለጻ፤ የትግራይ ሕዝብ በተደረገለት ድጋፍ እዚህ ደርሷል፤ ከዚህ በኋላ ደግሞ የሚፈልገው ነገር የሰላም ስምምነቱ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኖ በፈለገው ሁኔታ ወጥቶ ገብቶ ኑሮውን መኖር ነው፤ ይህ እንዲሆን ደግሞ መንግሥትና የክልሉ ሕዝብ እጅና ጓንት ሆኖ ሊሰራ ይገባል።

የትግራይ ሕዝብ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ክልል ነዋሪዎች በሰላም ወጥቶ እንዲገባ መሰረታዊ ፍላጎቶቹም እንዳይስተጓጎሉ ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል ያሉት ወይዘሮ አበባ አሁንም መሰረታዊ ፍላጎቶችን ወደነበሩበት ለመመለስ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባውም አመልክተዋል።

ከሽሬ የተጀመረው የመሰረታዊ ፍላጎቶች ጥገና ዛሬ ላይ ዓላማጣና መሆኒ እያለ አሁን በመላው የትግራይ አካባቢዎች ላይ የኤሌክትሪክ፣ የውሃና የምግብ እርዳታዎች እየተዳረሰ ነው። የህክምና መሳሪያዎችም ቢሆኑ ወረዳዎቹን በሙሉ እንዲሁም አይደር ሆስፒታል ላይ እየተሟሉ ነው። ይህ በጣም ጥሩና የሚያስመሰግን፣ መንግሥትንም ለስምምነቱ ያለውን ተገዢነት የሚያመላክት ነው ብለዋል።

አሁን በክልሉ ላይ የሰላም አየር እየነፈሰ ነው ያሉት ወይዘሮ አበባ፤ ሰዎችም ስለ ጦርነት ማውራት ትተው ስለ ሰላም መወያየት ጀምረዋል ብለዋል። ይህ በራሱ መልካም አጋጣሚ በመሆኑ እየተከናወኑ ያሉትን የመሰረታዊ ልማትና መልሶ ግንባታ ስራዎች ሕዝቡም በሚችለው መልኩ እንዲያግዝ መጠቀም ያስፈልጋል ሲሉም ጠቁመዋል።

"አሁን የትግራይ ሕዝብ ስለ ሰላም ማውራት ጀምሯል፤ ማውራትም ብቻ ሳይሆን መጻኢ እድሉን ማቀድም ይዟል፤ በመሆኑም ይህንን ጥሩ አጋጣሚ መጠቀምና መንግሥት የክልሉን ሕዝብ ደጀን አድርጎ ቀሪ ስራዎችን በፍጥነት ማጠናቀቅ፣ ህዝቡንም ተጠቃሚ ማድረግ ይኖርበታል " ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ አበባ ገለጻ ሕዝቡ ሙሉ ሰላሙ ተረጋግጦ የሌሎች ክልሎች ሕዝቦች ሳይቀሩ ክልሉ በአስተሳሰብ፣ በሰላም፣ በስራ እንዲለማ መደገፍ አለባቸው። ዋናውና ትልቁ ነገር የተባበረ የኢትዮጵያውያን እጅ ለትግራይ ሕዝብ ያስፈልጋል ብለዋል።

# የአገው ፈረሰኞች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ትስስራቸውን ይበልጥ እንዲያጠናክሩ የሚረዳ መሆኑን ገልጸዋል።

የአገው ፈረሰኞች ማህበር 62 ሺ በላይ አባላት እንዳሉት የገለጹት ዶ/ር ጋርዳቸው በዘንድሮው ፌስቲቫል ላይ ከ 5 ሺ በላይ ፈረሰኞች በዝግጅቱ ላይ ታድመዋል።

ፌስቲቫሉ ዓለምአቀፍ ቅርስ እንዲሆን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ እየተሰራ ነው ብለዋል። ለዚህም እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ በዩኒስኮ መስፈርት ሳይንሳዊ ጥናቶችን እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

በያዝነው ዓመት የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን ፌስቲቫሉን በማይዳሰስ ብሄራዊ ቅርስነት መመዝገቡ በዓለምአቀፍ ቅርስነት እንዲመዘገብ ትልቅ ሚና እንደሚኖረውም ገልጸዋል።

ፌስቲቫሉ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ እንደ አንድ የቱሪስት መዳረሻ እንዲያገለግል እየተሰራ ነው። በዚህም ዓመታዊ ፌስቲቫል ከማድረግ ባሻገር ኢትዮጵያ ውስጥ የፈረስ ግልቢያ የሚደረግበትና ሥልጠና የሚሰጥበት ትልቅ ማዕከል ለመገንባት የፈረስ ማህበሩ ከከተማ አስተዳደሩ ቦታ ተቀብሎ እየሰራ መሆኑን ዶ/ር ጋርዳቸው ገልጸዋል።

ፌስቲቫሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍ ያለ መሆኑን ገልጸው ለእንጅባራ ከተማም ትልቅ መነቃቃትን ፈጥሯል ነው ያሉት።

በእንጅባራ ከተማ ያሉ አገልግሎት ሰጪዎችን አበረታቷል በቀጣይም ባለሀብቶችን ለመሳብና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው አብራርተዋል።

የአገው ፈረሰኞች ማህበር የአገው አባቶች ከሌሎች አባት አርበኞች ጋር በመተባበር የጣሊያንን ወራሪ ኃይል አድዋ ላይ ድል መቀዳጀታቸውን ለመዘከር በየዓመቱ ጥር 23 በአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር የሚከበር በአል መሆኑ ይታወቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለውጡ ለዜጎች የዜግነት ክብር ምንጭ እንዲሆን ሁሉም ኃላፊነቱን ይወጣ !

ለውጥ በብዙ ገፊ ምክንያቶች የሚከሰት ማኅበረሰባዊ ክስተት ነው። በአግባቡ እና በጥንቃቄ ካልተገራ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ከተስፋው በላይ የከፋ እንደሚሆን በታሪክ በብዙ አጋጣሚዎች ታይቷል። ለዚህ ደግሞ እኛ ኢትዮጵያውያን ያሳለፍናቸው የለውጥ ታሪኮች ተጨባጭ ማሳያዎች ናቸው ።

በኢትዮጵያ ታሪክ በተለይ ከ1950ዎቹ ጀምሮ( በታሪክ የጄነራል መንግሥቱ ግርግር ከሚባለው) እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጦችን ታሳቢ ያደረጉ አገራዊ የለውጥ ንቅናቄዎች ተካሂደዋል።

የ 1950ዎቹ የለውጥ መሻት መፈንቅለ መንግሥትን ታሳቢ ያደረገውም ሆነ በ1960 ዎቹ ፣ አጠቃላይ አገራዊ የሥርዓት ለውጥን መሰረት አድርጎ የተካሄደው የለውጥ ንቅናቄ የታሰበላቸውን ዓላማ ሳያሳኩ አገርን ሕዝብን ብዙ ዋጋ አስከፍለው አልፈዋል።

በ1983 ዓ.ም በትጥቅ ትግል ፍጻሜ ያገኘው የኢህአዴግ የለውጥ ንቅናቄም የተከፈለለትን ከፍ ያለ ዋጋ ያህል አገርና ሕዝብን በተጠበቀውና በታሰበው መልኩ ተጠቃሚ ሳያደርግ በሌላ ሕዝባዊ የለውጥ ማእበል ተወግዶ ዛሬ ላይ በሌላ የለውጥ ምዕራፍ ውስጥ እንገኛለን ።

በመሰረታዊነት ለውጥንና የለውጥ ንቅናቄዎች በብዙ ገፊ ምክንያቶች ከመከሰታቸው አንጻር ፤ የለውጥ ኃይሉ ለእነዚህ ምክንያቶች ትኩረት በመስጠት ለለውጡ ስኬት ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስና ቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

ይህ የለውጡን ገፊ ምክንያት ከመረዳት የሚነሳው፤ ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ ፣ የሕዝብን ሁለንተናዊ ተሳትፎ መሰረት ባደረገ መልኩ የሚከናወነው የለውጥ ስራ በብዙ መልኩ ለፈተና የተጋለጠ እንደመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ ነው።

በአንድ በኩል ለውጡ በጥቅማችን ላይ መጥቷል ብለው የሚያምኑ፤ በሌላ በኩል በለውጥ ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉ ብዥታዎችን የፖለቲካ መቆመሪያ ካርድ አድርገው ለመጠቀም የሚፈልጉ ኃይሎች የለውጡ ዋነኛ ፈተና የመሆናቸው ጉዳይ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

እነዚህ ኃይሎች ፍላጎታቸውን በራሳቸው ማስፈጸም የሚያስችል አቅምም ሆነ ሕዝባዊ መሰረት የሌላቸው በመሆኑ፤ ለለውጡ ፈተና የሚሆነውን ፍላጎታቸውን እውን ለማድረግ ትልቅ አቅም አድርገው የሚወስዱት የለውጡ ኃይል የሆነውን ሕዝብ የለውጥ ተስፋ ከልቡ በማውጣት ወይም በመስረቅ ነው።

ይህ እውነታ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በተጨባጭ በአደባባይ የሚታይ እውነታ ከሆነ ውሎ አድሯል። እነዚህ ኃይሎች አገር ስለ ብልጽግና ተስፋ ሰንቃ መንቀሳቀስ መጀመሯን ተከትሎ ለኢትዮጵያ ዕድገት መሰረት የሆነውን አገራዊ ሰላም በመናጥ ዜጎች በለውጡ የሰነቁትን ተስፋ ለማስጣል ረጅም ርቀት ሄደዋል።

በዚህም ሕዝባችን እንደአገር ለሰነቀው ተስፋ ከፍያለ ዋጋ ለመክፈል ተገድዷል፤ በገዛ ህልሙ ፈቺ ሳያጣ ግራ እንዲጋባና ህልሙ ቅዠት ፤ተስፋው ደግሞ እርግማን እስኪመስለው፤ ዛሬ ብቻ ሳይሆን መጪውም ጊዜ እንዲጨልምበት ብዙ ተሰርቶበታል።

ሕዝባችን እንደ ሕዝብ ከመጣበት የለውጥ ወቅት ተሞክሮ አንጻር አሁን እየሆነ ያለው አገራዊ እውነታ መልኩና አካሄዱ የተለየ ቢመስልውም፤ ዋነኛ የአስተሳሰብ መሰረቱ ለውጡን በመቀልበስ ወደ ትናንቶች ሕዝባችንን መመለስ መሆኑ ብዙም የሚሰወር አይደለም።

አሁን ላይ እንደ ሕዝብ እየከፈልነው ያለው ከፍያለ ዋጋም ቢሆን በለውጡ ለሰነቅነው ተስፋ ስኬት ልንከፍለው የተገባ፤ አገርን ከትናንት ወደ ዛሬ ከማሻገር ባለፈ ትውልዶችን ከተንሰላሰሉ ትናንቶች በመታደግ፤ ዛሬያቸውን በአግባቡ እንዲኖሩ የሚያስችል ነው።

ታሪክ እንደሚዘክረው በየትኛውም ወቅት እና የዓለም ክፍል የተካሄዱ የለውጥ ንቅናቄዎች ያለ መስዋእትነት ስኬታማ አልሆኑም። የለውጥ ንቅናቄዎቹ ለስኬታቸው የጠየቁት መስዋእትነት ክብደትና ቅለት የሚመዘነውም ለውጡ በባለቤቱ በሕዝቡ ዘንድ በነበረው ግንዛቤ ነው።

ስለለውጡ የተሻለ ግንዛቤ የነበረው ሕዝብ በተሻለ መልኩ የለውጡ ባለቤት በመሆን ያለ በብዙ ዋጋ የለውጡ ትሩፋት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ከዚህ አንጻር መላው ሕዝባችን የለውጡ ባለቤት ከመሆኑ አንጻር ፤ለውጡ ከተገዛበት መርህና እንደ አገር ይዞት ከመጣው ተስፋ ላይ ዓይኑን ሳያነሳ ፤ ከሚነፍሱ አሳሳችና አዘናጊ የጥፋት ንፋሶች ከመወሰድ ተቆጥቦ እያንዳንዷን የለውጥ እንቅስቃሴ መከታተልና መደገፍ ይኖርበታል።

አሁን ላይ እንደ አገር ከለውጡ ጋር በተያያዘ እየከፈልነው ያለውን ዋጋ ለመቀነስ ፤ ለውጡም ወደ ስኬቱ እንዲፈጥን፤ ተስፋነቱም የሚጨበጥ እውነታ ሆኖ ለዜጎች የዜግነት የክብር ምንጭ እንዲሆን ለውጡን በተገቢው መንገድ በአገራዊ አውዱ መረዳት ያስፈልጋል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ‹‹ዕፅ በአስደንጋጭ ሁኔታ...

ከ7 ኛው ገጽ የዞረ

ብር የሚገመቱ ወጪ ዕቃዎችን የተቆጣጠርንበት ነው። በ2014 ዓ.ም ደግሞ 836 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር የሚገመት ዕቃ የተቆጣጠርንበት ሲሆን፤ በ2015 ዓ.ም በስድስት ወር ብቻ አንድ ቢሊዮን 184 ሚሊዮን ብር የሚገመት የተለያዩ ለምሳሌ የግብርና ምርቶች፣ ማዕድናት እና የቁም እንስሳት እንዲሁም የፋብሪካ ውጤቶች እና አደንዛዥ ዕፅን ጨምሮ ለመያዝ ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- ከአገር ደህንነት እና ኢትዮጵያ በቀጣናው ላይ ካላት ታሪካዊ ጠላቶች አንፃር እንዴት ይታያል? ብዙ አገራት በኮንትሮባንድ ንግድ በአሸባሪዎች አደጋ ላይ ወድቀዋል። በዚህ ደረጃ አይተነዋል?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** በእርግጥ አይተን ተንትነነዋል። ለምሳሌ በጦርነቱ ወቅት በየአቅጣቸው የተያዙ የጦር መሳሪዎችን ማየት እጅግ የሚያስገርም ነው። ለመሳሪያዎች ብቻ ራሱን የቻለ ትልቅ ሰነድ አለ። በሌላ በኩል አደንዛዥ ዕፁ ብቻውን ራሱን የቻለ ሰነድ አለ። ሌሎችም ለንግድ ሥራ የሚውሉ ዕቃዎችን የያዘ ሰነድ አለ። አደጋው በጣም ትልቅ ነው። የዚህ ዋናው ምንጭ የማይጠረቃ የኮንትሮባንዲስቶች ፍላጎት ነው። ምክንያቱም ኮንትሮባንዲስቶች ከሕጋዊነትን ይልቅ ሕገወጥነትን ይመርጣሉ።

ሕገወጥነትን ለምን ይመርጣሉ፤ ሲባል አንደኛ ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፍሉ ትርፍ ለማግኘት ነው። ጤናማ ያልሆነ መስመርን እንደአንድ የመክበሪያ ዘዴ በመቁጠር፤ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ታክቲኮችን ይጠቀማሉ።

አንደኛው ቦርደሩ ሰፊ ሲሆን ተቋማቶቻችን ደግሞ ደካማ ናቸው። ይህ ዕቃዎችን ለማውጣትም ሆነ ለማስገባት ይጠቀሙበታል። የፌዴራል ተቋማት በወረዳም ሆነ በዞን እንዲሁም በክልልም ሆነ በከተማ ያሉ የመንግሥት ተቋማት በዚህ ደረጃ ተከታትሎ ለማስቆም የሚያስችል ብቁነት የላቸውም። ይልቁኑ በተቃራኒው በመረጃ ወይም በማስተላለፍ ኮንትሮባዲስቶችን መመገብ እና እንዳይጠየቁ በማድረግ ይደግፏቸዋል።

ተቋማት አቅማቸውን ተጠቅመውና ተጠናክረው ሥራቸውን መስራት አለባቸው። ይህ አደጋ በመከላከል በኩል ያላቸው ድርሻ ተከታታይነት እና ተመሳሳይነት የለውም። ብቃቱም የለውም። የሚያዙትም ተመጣጣኝ ቅጣት አያገኙም። በስድስት ወር ብቻ 700 ኮንትሮባንዲስቶች ለሕግ አቅርበናል፤ እነዚህ በሕግ በአግባቡ መጠየቅ ነበረባቸው። ግን እዚህ ግባ የሚባል ቅጣት አላረፈባቸውም። የተያዙት እጅ ከፍንጅ፤ ከምስክሮች ጋር ነው። ግን በተገቢው ካልተመረመሩ ገቢ የክስ ቻርጅ አይደርሳቸውም። ክስ ተገቢ ክስ ካልቀረበ ደግሞ ዳኝነቱ ለመቅጣት ይቸገራል። እነዚህ ነገሮች ተዳምረው ኮንትሮባንዲቶች ጥርስ አውጥተዋል።

ገበያው ደግሞ ክፍት ነው። ወደ ገበያ የምናቀርበው ምርት እጥረት አለ። የኑሮ ውድነት ላይ ኮንትሮባንዲቶች አሉ፤ ያያሉ። እነዚህ አካላት በሕጋዊ መንገድ የሚገባውን ያውቃሉ። ገበያውን የሚያሟላ ባለመሆኑ ይህን ክፍተት ለመጠቀም ቀረጥና ታክስ የማይከፍሉበትን እቃ ወደ ገበያ በቀላሉ ያስገባሉ። በአሻጥር የሚያግዛቸው አካል ፈልገው እና አሳቻ ወቅት ተጠቅመው ወደ ገበያ ይገባሉ። እነዚህ አካላት ሕጋዊ ነጋዴም በመጣል ለራሳቸው በገበያው ላይ ይነግሳሉ። እነዚህ ሁሉ የገበያ ሥርዓቱን ማየትና ማረም አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል።

እፅ በአስደንጋጭ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ እየገባ ነው። በየብስ እና በአየር እየመጣ ነው። በአገር ውስጥ ደግሞ ካናቢስ እየተመረተ ነው። ይህ በጣም በከፍተኛ ደረጃ አደንዛዥ እፅ ወደ ኢትዮጵያ እየተጋዘ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዕፅ ዝውውር ለኢትዮጵያ አደጋ ደቅኗል ማለት ነው?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** አዎ! በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ደቅኗል። ሌሎች አካላት ዳታው ቢጠቀሙበት ጥሩ ነው። ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ ያመጣል። በተለይ ጤና ላይ የሚሰሩ አካላት ቢሰሩበትና ቢመራመሩበት መልካም ነው። በርካታ ቤቶች በዚህ ጉዳይ ለማህበራዊ ምስቅልቅል ነው። ተሸፍኖ ይሆናል እንጂ በርካታ ቤተሰቦች በዚህ ጉዳይ ታውከዋል። በየትምህርት ቤቱም አደገኛ ሁኔታ ላይ ነው። ይህ ለኢንቨስትመንቱ፤ ለምርታማነትና ለገበያ አደገኛ ሁኔታ ላይ ይጥላል። በአጠቃላይ ሕግ ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ፣ ዕጽ ለአገሪቱ በጣም አደጋ ደቅኗል። በመሆኑም ከታችኛው እርከን ጀምሮ የሚመለከታቸሸው የመንግሥት አካላት ትኩረት ሰጥተው መሥራት አለባቸው። ቴክኖሎጂ መጠቀም፤ እርምጃ ማጠንከር፤ ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር ለይደር የማይተው ጉዳይ ነው። የሚመለከተን ሁሉ ሥራችን ነው ብለን ካልሰራን ይህ ከፍተኛ አደጋ ያስከትላል፤ ማህበረሰባዊ ቀውስም ያስከትላል። በእኛ በኩል በጣም በትኩረት እየሰራን ነው። በዚህ ሂደት ብዙ ሰው አጥተናል። በርካታ ባለሙያዎችና የፀጥታ አካላት ሞተዋል፤ አካል ጎድሏል።

አንዳንድ ኮንትሮባንዲስቶች ቀላል አይደሉም። በመኪና ሰው ይገጫሉ፤ ተዋግተው ኬላ ይጥሳሉ፤ በርካቶችን ገድለው ያልፋሉ። ይህ ደቡብ አሜሪካ እና ጣሊያን ያየነው ማፊያ ቡድን የበቀለው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው። በመሆኑም አደጋው አሳሳቢ በመሆኑ በጋራና እና በፅናት ልንዋጋው ይገባል።

ለምሳሌ ማዕድንን ብንመለከት ማግኘት ከሚገባን ገቢ 63 በመቶ ቀንሷል። በጫት ላይ ከፍተኛ ትንቅንቅ አለ። በየቀኑ ከፍተኛ የሆነ ጫት መጠን ይቃጠላል። ይህን አደጋ ለመከላል የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በቁርጠኝነት ካልሰሩ እና ሁሉም ኃላፊነቱን ካልተወጣ በጣም ፈታኝ ነው። እጅና ጓት ሆኖ የሚሰራ አካል ካለ አገር ትዳከማለች። የአገር የነውጥ አንዱ ምንጭ ይሆናል። ሕገ ወጦች ሲነግሱ ሕግ ይነጥፋል። ስለዚህ ሕግ ትርጉም አልባ ይሆናል። ጉልበተኞች እንደፈለጉ ከሆነ ትውልድ አደጋ ላይ ይወድቃል። ወደዚህ ምዕራፍ እንዳይደርስ በትጋት መሥራት ይገባል። በአሁኑ ወቅት ኮሚሽኑ፣ በየደረጃው ያሉ የፀጥታ መዋቅሮች፣ የአገሪቱ የደህንነት ተቋማት በመናበብ እየሰሩ ነው። ግን በቂ አይደለም፤ ገና ብዙ መሥራት አለብን። መከላከልና መቆጣጠር ሥራችን ተጠናክሮ ይቀጥላል።

የኮንትባንድ ሥራ በሚዲያ አዋጅ እና በአንድ ቀን ስብሰባና አይፈታም። በፎቶ ሾው ኮንትሮባንድ መካለከል አይቻልም። ኮንትሮባንድ ቀን ከሌሊት ስለሚኖር የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ተደራጅተውና ተናበው መሥራት አለባቸው። ገቢ ንግድ ሥርዓታችን በተመለከተ በስድስት ወር የተገኘው 90 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ታስቦ 87 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ተሰብስቧል።

ይህ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 34 ቢሊዮን ብር ብልጫ አለው። ኤክስፖርትን በተመለከተም ባለፉት በስድስት ወራት ውስጥ አንድ ቢሊዮን 554 ሚሊዮን ዶላር በላይ ተገኝቷል። በስራ ሂደት ውስጥ ብልሹ አሰራር ውስጥ የገቡ ሰራተኞችን ከሥራ እስከማሰናበት የተወሰነ ውሳኔ ተወስዷል። በዚህ ስድስት ወራት ብቻ 446 አመራሮችና ሰራተኞች ላይ እርምጃ ተወስዷል።

**አዲስ ዘመን፡- ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ኮሚሽኑ ምን እየሰራ ነው?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** በዚህ ላይ በስፋት እየሰራን ነው። ለአገር መከላከያ ሠራዊት፤ የአቅመ ደካሞችን ቤትና የምገባ ማዕከላት መገንባት፣ ገበታ ለአገር፤ ሸገር ፕሮጀክት እና ሌሎችም ላይ በሰፊው እየሰራ ነው።፡ በዚህ ረገድ በስድስት ወራት ብቻ 524 ሚሊዮን ብር የሚገመት ቁሳቁስና በገንዘብ ደረጃ የማህበራዊ ኃላፊነት ተወጥቷል። ከሪፎርሙ ወዲህ ደግሞ ስምንት ቢሊዮን ብር ለማህበራዊ ኃላፊነት ተወጥቷል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ስነበረው ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ አመሰግናለሁ።

## ተጠየቅ

# ‹‹ዕፅ በአስደንጋጭ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ እየገባ ነው››

- አቶ ደበሌ ቀበታ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር



ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**በተለያየ ጊዜ የተለያየ ስም ቢሰጠውም ተቋሙ ግን አንጋፋ ነው። ለ134 ዓመታት አንድ ጊዜ ከሌሎች ተቋማት ጋር እየተቀላቀለ፤ ሌላ ጊዜ እራሱን ችሎ የኖረ ተቋም ነው። ኢትዮጵያ ተቋማትን ከመገንባት አንጻር ረዥም እድሜ ያስቆጠረች ብትሆንም በአሠራር፣ በአደረጃጀት፣ በቴክኖሎጂ፣ ተቋማት በሚሰጧቸው ፍትሃዊ አገልግሎቶች ጠንካራ የሚባል ተቋም ሳትገነባ የኖረች አገር ነች። ታዲያ በዚህ ውስጥ ካለፉት ቀዳሚ ተቋማት መካከል ጉሙሩክ ኮሚሽን አንዱ ነው። የተቋሙን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ከጉሙሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቀበታ ጋር ቆይታ አድርገናል።**

**አዲስ ዘመን ፡- ኮሚሽኑ በዋናነት የሚሠራቸው ሥራዎች ምንድን ናቸው? በተለይ ከሪፎርም ጋር ያሉ ጉዳዮችን አስመልክቶ አንኳር የሚባሉቱን ቢያነሷቸው?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** የኮሚሽኑ ዋና ዋና ተልዕኮዎች ተብለው የተቀመጡት በርካታ ናቸው። ከተልዕኮዎቹ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል አንደኛው የኢትዮጵያ ገቢና ወጪ ምርቶችን የጉምሩክ አገልግሎት መስጠት ነው። ሁለተኛው የገቢ ንግድ ሥርዓቱ የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት የመፈጸሙ ጉዳይ ነው። ሦስተኛው ደግሞ ኮንትሮባንድና ሕገ-ወጥ ንግድን የመቆጣጠር ሥራን መሥራት ነው። በተለይ ኮንትሮባንድና ሕገ-ወጥ ንግድ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ጫና ስለሚታወቅ አስቀድሞ የኮሚሽኑ ትልቁ ተልዕኮ ተደርጎ በሕጉ የተቀመጠ መቋቋሚያ ደንቡ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ኮሚሽን ባደረጋቸው ሪፎርሞች ምን ለውጦች መጡ?**

**ኮሚሽነር አቶ ደበሌ፡-** ኢትዮጵያ በመንግሥት ምስረታ ረዥም ዓመታትን ያስቆጠረች አገር ናት። በዚህ ረገድ ረዥም እድሜ ካስቆጠሩ አገራት ተርታ ትሰለፋለች። ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ገና መንግሥት የሚባል አስተዳደርና ተቋማትን ከመሰረተች ጊዜ ጀምሮ ሰባት ቁልፍ ከሚባሉ ተቋማት መካከል አንደኛው ጉምሩክ ነው። እንግዲህ ከዛሬ 134 ዓመት በፊት ቁልፍ የሚባሉ የመንግሥት ተቋማት ሲመሰረቱ አንዱ የጉምሩክ ተቋም ነበር። ስሙ አንዳንድ ጊዜ በጅሮንድ፣ አንዳንዴም ጉምሩክ፣ አንዳንዴም ጉምሩክና ኤክሳይዝ በሚል ተቀያይሯል።

አንድ ሥርዓት ሲመጣ የነበረውን ያፈርስና ከዜሮ ይጀምራል ፤ ሌላው ሥርዓት ሲመጣም ተመሳሳይ ድርጊት ይፈጽማል፤ እንዲህ አይነት አዙሪት ውስጥ የኖርን በመሆናችን ምክንያት ጠንካራ ተቋማትን ሳንገነባ ኖረናል። ይህ ደግሞ ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት የባሰበት ነበር። በሪፎርሙ ምን ተሠራ? የሚለውን ለማየት ዳራዎችን መመልከት ጠቃሚ ስለሆነ ነው ከኋላ የተነሳነው። ኢትዮጵያ ጠንካራ ተቋም መገንባት ያቃታት ለምንድን ነው? የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ አድርገን ነው የተነሳነው።

መከላከያን ጨምሮ ከሰባቱ ዋና ዋና ተቋማት ውስጥ ጉምሩክ አንዱ ነው ከተባለ ለምንድነው ጠንካራ የጉምሩክ ሥርዓት መገንባት ያልተቻለው? የሚለውን ጥያቄ በ2010 ዓ.ም መዳረሻ እና በ2011 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ መነሻ በማድረግ ወደ ሪፎርም ገብተናል። ስለዚህ በአንድ ጊዜ በርካታ የሪፎርም አጀንዳዎችን በማከናወናችን ለውጥ መጥቷል።

የኢትዮጵያን የተቋማት ግንባታ ስብራትን ሊጠግን የሚችል ጠንካራ ተቋም መገንባት ካለብን የምንገነባውን ተቋም ራዕይ መንደፍ ያስፈልግ ነበር። በዚህ መነሻነት የኢትዮጵያ ጉምሩክ የተጠቀሱትን ከላይ የተዘረዘሩ ተልዕኮዎች ለመወጣት ኢትዮጵያውያን የሚፈልጉት ተቋም አድርጎ መገንባት በጣም ያስፈልጋል። ስለዚህ በአንድ ጊዜ በጣም በርካታ የሪፎርም አጀንዳዎችን አብሮ ማካተት ነበረብን። በራዕይ ደረጃ ያስቀመጥነው በ2025 ዓ.ም ኢትዮጵያውያን የሚያምኑትና የሚተማመኑበት በሁለንተናዊ አቅም የተገነባ ፣ ለዜጎች ፍትሐዊ አገልግሎት መስጠት የሚችል፣ ኢትዮጵያውያንን የሚያረካ የጉሙሩክ ተቋም ገንብቶ ማየት የሚል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በስትራቴጂ እቅዱ ላይ የተቀመጠው ማለት ነው?**

**አቶ ደበሌ፡-** አዎን! ይህንን በሚገባ መለየት አስፈላጊ ነው። ከጎደሉት ጉዳዮች አንዱ ይህ ነበር። ጠንካራ ተቋም እንገንባ ከተባለ የምንገነባው ተቋም በ2025 ዓ.ም በራዕያችን ልንገነባ ያሰብነውን ተቋም ለማየት በሚገባ ትኩረት ለማድርግ ተሞክሯል። ስለዚህ ኢትዮጵያውያንን ያረካ ፣ በሁለንተናዊ አቅሙ የተገነባ፣ ማለትም በሰው ኃይል፣ በተቋም፣ በስትራቴጂ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተደራሽነት ወዘተ ጠንካራ ተቋም ገንብቶ ማየት የሚል ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ዝርዝር ስትራቴጂዎች ያስፈልጋሉ። የስትራቴጂ ዶክመንት ማዘጋጀትና በግልጽ ማስቀመጥ በራሱ አስፈላጊና አንዱ የጎደለ ነገር ነበር።

ይህን ተከትሎ የአስር ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ተዘጋጅቷል። እንግዲህ የተገኙት ውጤቶች ምንድን ናቸው? ከተባለ አንዱ ይህንን ስትራቴጂክ ሰነድ ወደ ሥራ ማስገባት፤ ይህም ብቻ ሳይሆን ኮሚሽኑን የሚመጥንና እናስገኛለን የተባለውን እድገት የሚመጥን መዋቅር ማስቀመጥ አንዱ የሪፎርሙ አካል ነበር። እናስገኛለን ያልነውን እድገት የሚመጥን እሱን ሊያሳካ የሚችል መዋቅር ማስቀመጥ ነበረብን። ይህ አንዱ የሪፎርሙ አካል ነው።

የጉምሩክ ሥራ በጣም የተወሳሰበ ስለሆነ ይህም ውስብስብ የሆነውን የሥራ አካባቢ ወይም ባህሪን ሊሸከም የሚችል መዋቅር ምን አይነት ነው? ለተገልጋይ ተደራሽ ሊሆን የሚችል፣ በየሥራ ባህሪያት እና አገልግሎቱ ባሕሪያት የሚተነተን ነው። በቅርንጫፍ ደረጃ ከቅርንጫፍ ውጭም ያሉት ምን አይነት አደረጃጀት ይኖረናል የሚለው በደንብ መጤን አለበት። ምክንያቱም በአገር ውስጥ በጣም በርካታ ኢትዮጵያን በሙሉ የሚያካልል አገልግሎት የሚሰጥ ስለሆነ ኬላዎችን ጨምሮ፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን፣ በሁሉም አገር ውስጥ ባሉ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እና በድንበሮቻችን ዙሪያ ከኢትዮጵያ ውጭም ባሉን ሁለት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እንዲሁም ወደፊት የሚከፈቱትን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ጨምሮ ይሄንን ግልጽ ማድረግና የተዘረዘረ ሥራ ማስቀመጥ በጣም ጠቃሚ ስለነበር አንደኛው ትልቁ ሥራ ይሄ ነበር። ራሱን ችሎ በጣም ጥልቅ ሥራና ትልቅ ጊዜ የጠየቀ ስለነበረ ሪፎርሙን የሚሸከመው ይሄኛው መሰረት ነው።

መዋቅሩ ካስቀመጥን በኋላ ደግሞ መዋቅሩ ላይ የሚመደበው የሰው ኃይል እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል። መቅጠር፣ ማሰልጠን፣ ማብቃት፣ ማሰማራት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ውጤታማነቱን በዛው እግረ መንገድ ስለሚለካ ነው። ስለዚህ መዋቅር መፍጠር ብቻ ሳይሆን መዋቅሩ ላይ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ በሁሉም አቅጣጫ፣ ቦታዎች፣ የጉምሩክ አገልግሎት መስጫ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ማዘጋጀት የግድ ነው። ኬላዎች፣ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ድንበሮች በእነዚህ ላይ ደግሞ በመዋቅሩ በተተነተነው መልክ የሰው ኃይሉን መመደብ፣ ማሰልጠን፣ ማሰማራት፣ መከታተል፣ መደገፍ፣ መሸለም፣ መቆጣጠር የመሳሰሉ ሥራዎች ደግሞ የእዚህ ማዕቀፍ አካል ሆነው እየተሠሩ ነበሩ።

ስለዚህ በተቋሙ መዋቅር እና በተቋሙ የሰው ልማት (human development) ዙሪያ የሠራናቸው ሥራዎች በጣም ውጤታማ ነበሩ። አንደኛው ወሳኝ ሥራ ይሄ ነው። ሁለተኛው ጉምሩክ በባሕሪው አገልግሎት የሚሰጥባቸው የስራ አካባቢዎች አንደኛ ከስፋቱ አንጻር እና የሥራ አካባቢው ውስብስብነት በጣም ትልቅ ነው። ስለዚህ ለሁለት ነገሮች በሚገባ መገዛቱን ማረጋገጥ አለብን። አንደኛ የአገር የወደብ (port) ፍላጎት አለ። ጉምሩክ የተሰጠውን አገልግሎት በብቃት እንዲያገለግል የመንግሥት የወደብ (port) ፍላጎቶች አሉ። መንግሥት የሚከተለውን የሪፎርም አጀንዳ (የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ ሊሆን ይችላል) ስለዚህ ቀጥታ የኢምፖርትና የኤክስፖርት አገልግሎቱ ደግሞ ለእነዚህ የመንግሥት ፖሊሲዎችና የመንግሥት ፍላጎቶች ቀጥታ አወንታዊም አሉታዊም ተጽኖ አለው።

ስለዚህ አንደኛው ይሄንን የሚሸከም አሠራር ሊኖር ያስፈልጋል። ሁለተኛ ይሄ ብቻ ሳይሆን ደግሞ ዓለምአቀፋዊ በሆነ ሁኔታ ዓለም አቀፍ የጉምሩክ ሥርዓቶች ደግሞ አሉ። ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የጉምሩክ ህብረት አባል ስለሆነች ከዚህ አኳያ የሚፈለግብን ወይም የሚጠበቅብን ሥራ አለ። የምናወጣቸው ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሠራሮች በሙሉ ለዓለም አቀፍ የጉምሩክ ህብረት ሥርዓት (vena convention or revised croton convention) የተገዛ የሕግ ማዕቀፍና ሥርዓቶች ሊኖሩን ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- በርፎርሙ ከተሰሩ የኢትዮጵያን ጥቅም ማስጠበቅ ዓለም አቀፍ ሕጎች እና ድንጋጌዎችን መጠበቅ አንዱ ነው። ኢትዮጵያን በቀጣናው ወደብ የሌሳት አገር ናት። በዚህ ሳይ ምን እየተሰራ ነው?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ከአወቃቀሩ ጀምሮ ለምሳሌ ነገ ኤርትራ ወደቦች ላይ አገልግሎት የምንጀምር ቢሆን ኤርትራ ወደቦች ላይ የኢትዮጵያ ጉሙሩክ ሊሰጥ የሚችለውን አገልግሎት አስቀድመን እኛ በለውጥ ሂደት ሰርተነዋል። ሊኖረን የሚችለውን የትራንዚት ፕሮቶኮል የሰራነው በ2010 እና 2011 ነው። ስለዚህ ያለው እስትረቴጅክ ዕቅዱ በስፋት ነው። ከሁለቱም ሱዳን እና ከኬንያ ጋር የሚኖረንን ከጅቡቲ ጋር ከሶማሊያ ታሳቢ ተደርጓል።

የኢትዮጵያን ጥቅም እንዴት ማስጠበቅ ይቻላል፤ ከዛም ባለፈ በዓለም አቀፍ ንግዱ ውስጥ ምንድን ነው? የኢትዮጵያ ጥቅሞች ለምሳሌ ነገ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ብትሆን የጉሙሩክ አሠራርን ማፋጠኑን በመጨመር ሊያመጣቸው የሚችሉ አገልግሎቶች የተባሉት በሙሉ ኢትዮጵያ በየጊዜው የምትፈራረማቸው ስምምነቶች አሉ። ጉዳዮች በተለያየ መንገድ ይተነተናሉ።

በትራንዚት ሥርዓት ውስጥ አንድ ተጓዥ ከጀርመን ተነስቶ ኢትዮጵያ ውስጥ የምናስተናግደው ስመጣ እንዴት ነው? የእኛ ከስተምስ ሊያገለግል የሚችለው እንዴት ነው? የዋስትና ጉዳዮች ቢያጋጥሙ ማለትም ድንበር ዘለል የሆኑ የዋስትና ጉዳዮች ቢያጋጥሙ መሰል ነገሮችን አንድ በአንድ ለቅሞ ነው የሰራው። ኢትዮጵያ ከተለያዩ አገራት የምታስገባቸውም ሆነ ወደ ውጭ የምትልካቸው ዕቃዎች ጎሮቤቶቻችን ላይ ያሉ ወደቦችን በትክክል በመጠቀም በተለይ የእኛ የማመቻቸት እና የቁጥጥር ሥርዓታችንን የዘመነ የተተነተነ መሆን አለበት።

የዜጎችን መብት የገፉ፤ አንቀጾችን በሙሉ በማስወገድ በአዲስ መልክ ያሻሻልናቸው አሉ። ለአብነት ከስተምስ አዋጅ ማሻሻያ 1160/2011 በዚህ የሪፎርም አጀንዳ ሂደት ውስጥ የሠራነው አንዱ የሕግ ማዕቀፍ ነው። ከዛ በኋላ በጣም የተተነተኑ ስድስት ደንቦችን አንድ ላይ ያጠቃለለ የጉምሩክ ደንብ የተተነተነ ነው።

በጣም በርካታ ፕሮሲጀሮች አሉ። እነዚህ ፕሮሲጀሮች ትራንዚት ለማሳለጥ የመጋዘን አገልግሎትን ለማቀላጠፍ፤ ክሪላንስን ለማሳለጥ ወጪም ገቢን የክሪላንስ ሥርዓቶችን ለማሻሻል የተወሰዱ ናቸው። ይሄን መሥራት ብቻውን በቂ ስላልሆነ የሰው ሃይሉን ማሰልጠን ማብቃት ያስፈልጋል። አሁንም ይሄ ብቻውን በቂ አይደለም። የምንሰጣቸው አገልግሎቶች በጊዜ የተለኩ መሆን አለባቸው።

እያንዳንዱ በኢምፖርትም በኤክስፖርትም የምንሰጣቸው አገልግሎቶች የተለኩ እና ስታንዳርድ ያላቸው መሆን አለባቸው። በዛ መሰረት ደግሞ አገልግሎት የተሰጣቸው ስለመሆኑ እርካታን ያረጋገጠ ስለመሆናችው መለካት አለባቸው። ከአገልግሎት ተቀባዩ አንፃር መለካት አለበት። እንደዛው ደግሞ ከማናችንም ውጭ በሆነ መለኪያ በዓለም ባንክ (ኤልፒአይ or logistics performance index) በሚለው ዓለም አቀፍ መለኪያ ይለካሉ።

በተጨማሪ የኢትዮጵያ የጥራት ሽልማት ድርጅት ሁሉንም ተቋማት የሚለካበት በጣም በርካታ የተተነተኑ መለኪያዎች አሉት። እነዚህ የሪፎርም ሥራዎች ተቋማትንም ጭምር የሚለኩ ናቸው። አንድም በተገልጋዩ ይለካል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከኛ ውጭ ባሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ይለካል።

ሶስተኛ ደግሞ የኢትዮጵያ ተቋማትን የጥራት ደረጃ በሚለካ ተቋም ወይም በኢትዮጵያ የጥራት ሽልማት ድርጅት ይለካል ማለት ነው። በነዚህ ሁሉ የሪፎርም ሥራዎች ይለካሉ። በነዚህ ሁሉ መለኪያዎች ደግሞ ኮሚሽኑ ወደፊት እንደመጣና በየዓመቱ ተሸላሚ እንደሆነ እያየን ነው። ስለዚህ አንዱ የኦፐሬሽን ሥራዎቻችን የምንመራበት የሪፎርም ዝርዝር ወይም አጀንዳዎችን ሠርተናል። እዚህ ውስጥ አንዳንዱን ለመጥቀስ ያህል ቴክኖሎጂን እናንሳ፤ ከስተምስ ያለ ቴክኖሎጂ የትም ሊደርስ አይችልም።

አንዱ ባለፈው ሥርዓት ውስጥ የነበረው ስብራት ለውሳኔዎች ኢ-ፍትሃዊነት ለማጭበርበርም ለሌብነትም ለኢ-ተገማችነትም ለዜጎች የእንግልት ምንጭ ነበር። አገልግሎቶች የሚሰጡት በምን ልክ ነው በየትኛው ቴክኖሎጂ፤ የሚሉት ነገሮች አልተመለሱም ነበር። ሪፎርሙ ይህንን መልሷል። በቴክኖሎጂ ረገድ ከኢትዮጵያ ወደፊት ከሄዱ ተቋማት መካከል አንደኛ ሆኗል። ዛሬ

# ተጠየቅ



ኦን ላይን ከስተም አገልግሎት ወይም ወረቀት አልባ አገልግሎት ነው የምንሰጠው። ይህም በብዙ አካላት የተመሰከረ ነው። የተመሰከረበት አግባብ ደግሞ ይሄንን ሥርዓት እኛ ነን ያለማነው።

በቴክኖሎጂ ረገድ ብዙ ለውጦች መጥተዋል። ይህ በጣም ትልቅ ነው። የኢትዮጵያን የከስተምስ ማኔጅመንት ወይም አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ ስናደርግ አንደኛ ቢፒኤ (business analysis) እራሱ የኛ መሆኑ አንዱ ትልቅ ዲፓርቸር ነው። ሁለተኛ ሁሉንም አገልግሎቶች በዚህ ቴክኖሎጂ መስጠት ችለናል።

ሶስተኛ ይህ ቴክኖሎጂ የከስተምንም የአገልግሎት ሥርዓትንም በማረቅ የተገልጋዮችንም ጊዜ፣ ገንዘብና ሀብት በመቆጠብና የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ አንድ ትልቅ ዲፓርቸር ፈጥሯል። ዛሬም በመላ አገሪቷ በሙሉ ሰው ቤቱ ላይ ሆኖ ኮምፒተርና የእጅ ስልኩን ተጠቅሞ አገልግሎቱን የሚያገኝበት እድል ተፈጥሯል።

ሌላው አንዱ የሚያከራክረው ቴክኖሎጂ ውስጥ ለአብነት ዋጋ ነው። የዕቃዎች ዋጋ በዓለም ደረጃ አከራካሪና አጨቃጫቂ ነው። ከዚህ ቀደም እንደዚሁ በግለሰቦች ፍላጎትና ግምት ይሠራ ነበር። ትንሽ ሻል ባለመልክ ደግሞ ወደ ሲዲ የተቀየረበት (ዋጋዎች ከዓለም አቀፍ የዋጋ ምንጮች የተሰበሰቡ በሲዲ ተደራጅተው በሲዲ ላይ በተገለጸው ዋጋዎች ዋጋ ይወሰን የነበረበት)። ይሄንን በሌላ አሠራር ወይም ሪፎርም መተካት ያስፈልጋል። በዚህም በጣም ተገማች የሆነ ተአማኒና ሕጋዊ የሆነ አንዱ ከደንባችን ስለሚፈልቅ በደንባችን የዕቃዎችን ዋጋ የሚተምነው ጉምሩክ ነው ስለሚል እንዴት ነው። ይሄንን የምንተምነው ዝምብለን ሲዲውን ዲፐሊኬት እያደረግን ነው። የውስጥ ደግሞ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ አለብን የሚል ነው። ይሄ የኢሲቬስ ኢትዮጵያ ሥርዓት (Ethiopian customs variation system) ብለን የምንጠራው ቴክኖሎጂ አልምተን ዋጋዎችን በዚህ የቴክኖሎጂ መረጃ ቋት ላይ አደራጅተን አንድ ጊዜ በሁሉም ቅርንጫፎቻችን ኦን ላይን እነዚህን ዋጋዎች እያየ ባለሙያዎቻችን፣ የሥራ ኃላፊዎች ወዘተ አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ሥራ የሠራንበት በጣም አንዱ ትልቅ ሪፎርም ነው። ምክንያቱም ዋጋ እጅግ እጅግ መሰረታዊ ነገር ስልሆነ። ይህም በቴክኖሎጂ ከሚካተቱ ሥራዎቻችንና የሪፎርም አጀንዳዎቻችን አንዱ ነው።

ሌላው የአንድ መስኮት አገልግሎት (single window) የሚባለው ነው። በኮርያውያን በባለሙያም እንደገናም ደግሞ በካፒታልም የተወሰነ ድጋፍ ወይም ኢንጀክሽን አለን። ከዛ ውጭ ግን ሙሉ በሙሉ ቢዝነስ አናሊስሱ በኛ ነው የተሠራው። ዛሬ በጣም በርካታ የመንግሥት ተቋማትን በአንድነት ያሰባሰበ ከስተምስን በባለቤትነት የሚመራው የጉምሩክ አንድ መስኮት አገልግሎትን ሥርዓት ተግባራዊ ያደረግንበት ሁኔታ ነው ያለው።

የአደጋ አስተዳደር (risk manegment) ሥርዓት፣ እንደዚሁ ደግሞ በአሁኑ ሰዓት እያለማን ያለነው በቅርቡም ሥራ ላይ ልናውል የምንችለው የካርጎ ትራፊክ ሲስተም (cargo traffic system) አንዱ ቴክኖሎጂ ነው። ኢአይ (customs artificial intelligent) ቴክኖሎጂዎችን የተለያዩ ዲስትራክቲቭ ቴክኖሎጂዎችን የዚሁ አካል አድርገን ለመጠቀም እየሠራን ያለነው። በአጠቃላይ በቴክኖሎጂ ማዕቀፍ እጅግ እጅግ በሚያስደምምም ሁኔታ ለውጥ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- ቴክኖሎጂ በመጠቀማችሁ በቁጥር ሲገለፅ የሚችል የአገር ሀብት ማዳን ተችሏል?**

**ኮሚሽር ደበሌ፡-** በእርግጥ ይህ በየዓመቱ ይለካል። እኛ ብቻ ሳንሆን በኤልፒአይ (Logistics Performance Index) የዓለም ባንክ ባለሙያዎች እና ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ባለሙያዎች፣ ለምሳሌ ከእኛ ውጭ በሆኑ፣ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የሚያስተባብረው አካል ምን ውጤት እንዳመጡ ይለካቸዋል። ባለፈው ዓመት፣ በአንድ ዓመት ብቻ በዋጋ ደረጃ ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ማዳን የተቻለ መሆኑን በዘርፉ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ባለሙያዎች ያረጋገጡትና ምስክርነት የሰጡበት ነው።

አንደኛ ጊዜ ቆጥቧል። ሰው አገልግሎት ለማግኘት በርካታ የመንግሥት ተቋማትን ያማትራል። ለምሳሌ እስክሪብቶ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚፈልግ አካል የራሱ ስልክ ላይ ሆኖ ድክሌር ማድረግና ፍቃድ እና ማረጋገጫ ለማግኘት ወደ ተለያዩ ተቋማት መሄድ ሊጠበቅበት ይችላል። ስለዚህ ይህን ለማድረግ ከቤቱ ይወጣል፣ መኪና ካለው ነዳጅ ይመድባል፣ ጊዜ ይመድባል፣ እነዚህን ሁሉ አድርጎ በጊዜም ላያገኝ ይችላል። ስለዚህ ለኢምፖርተሮችም ለኤክስፖርተሮችም ከፍተኛ ጊዜ ቆጥቦላቸዋል።

ሁለተኛው ደግሞ በዚህ ምክንያት ያወጡ የነበረውን ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ ቆጥቦላቸዋል ብለን ነው የምናምነው። ሰው ከራሱ ኮምፒዩተር ላይ ሆኖ የሚፈልገውን እቃ ዲክሌር በማድረግ ከጉምሩክ አገልግሎት ማግኘት የሚያስችል አሰራር መንገድ ተፈጥሯል። ይህ ትልቅ ነገር ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ይህ ሪፎርም ከቴክኖሎጂ ወጣ ብሎ በጣም በርካታ ማሻሻያዎችን አድርጓል። ለምሳሌ ከዚህ ቀደም ግልጽ ያልነበሩ እጅግ በርካታ አሰራሮችን በማስወገድ ግልጽነትን ፈጥሯል። ለምሳሌ መረጃን ቀድሞ የማግኘት መብት። አንድ ሰው አንድ እቃ ከመምጣቱ በፊት ቀድሞ መረጃ ማግኘት ካለበት ጉምሩክን ጠይቆ አስቀድሞ መረጃ ያገኛል። ይህ ደግሞ ብዙ ነገር ያስቀርለታል። ‹‹ልግዛው›› ወይንስ ‹‹አልግዛው›› የሚለውን አስቀድሞ ለመወሰን ያስችለዋል።

መቻሉንና አለመቻሉን ወስኖ፣ የሚችል ከሆነ ይገዛዋል፤የማይችል ከሆነ ደግሞ ጊዜ ጠብቆ ይገዛዋል። ይህ አሰራር ከዚህ ቀደም አልነበረም። ምክንያቱም ሰዎች ይህን መረጃ ይደብቁና ይህን መረጃ ለመፈለግ ሲባል አላግባብ ይከፍላሉ። ስለዚህ ግልጽነትን በመፍጠርና ሰዎች የሚፈልጉትን መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ ረድቷል። ይህ አንዱ በሪፎርሙ ውስጥ የመጣው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የዓለም ገበያ በሚዋዥቅበት በዚህ ወቅት ጉምሩክ ገቢና ወጪ ምርት ላይ በሚሰራው ሥራ የኑሮ ውድነት በማቃለል ላይ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ አለው ተብሎ ይታመናል። በዚህ ላይ ኮሚሽኑ ምን እየሠራ ነው?**

**ኮሚሽር ደበሌ፡-** አንዱ ሥራችን አሰራሮችን ማፍታት ነው። ይህ ደግሞ የዜጎችን ጊዜ እና ገንዘብ በመቆጠብ ሚና አለው። በዚህ ላይ ንቁ ሆኖ መስራት ይገባል። አሰራርና ሂደት፣ ደንብና መመሪያ ብሎም እያንዳንዱ ተግባር በዜጎች ላይ የራሱ የሆነ ሚና አለው ብለን እየሰራን ነው። በግልጽ ለመናገር እኛም በዚህ ደረጃ በዝርዝር እየሰራን ነው። ለምሳሌ ከሪፎርሙ በፊት የነበረው አዋጅ 622 ነበር። ይህን ተከትሎ ደግሞ ሌላ አዋጅ ነበር። እነዚህ የየራሳቸው ጥቅምና ድክመት ነበራቸው። በ622 እቃ ደረቅ ወደብ ለይ የሚቆይበት ጊዜ አያስቀምጠውም።። በመሆኑም በሪፎርሙ በአዋጁ ያካተትነው 829 ነበር። እቃ ወደብ ላይ ሲቀመጥ በቆየ ቁጥር ጊዜ ይገዛበታል፤ በዚያውም እየተወደደ ይሄዳል። በተጨማሪም የተለያዩ ወጪዎች ስለሚኖሩ በወደብ ላይ ባለው ቆይታ የሚኖረውን ወጪ አስመጪዎች ተጠቃሚዎች ላይ ይጭናሉ። ይህን ገምግመን መፍትሄ አስቀመጥን። በመሆኑም በደረቅ ወደብ ተጓጉዞ የመጣ ዕቃ በ15 ቀናት ውስጥ ወደ ገበያ አሊያም ልማት መግባት አለባቸው።

በካርጎ ተርሚናል ወይም በአየር መንገድ በኩል የመጣው ደግሞ መቆየት ያለበት 10 ቀናት ብቻ መሆን እንዳለበት በአዋጅ ጭምር የተቀመጠ ነው። ይህን ስንወስን ደግሞ የምንሰጠው አገልግሎት መስጠት አለብን። ለምሳሌ እቃ ወደብ ላይ ሲደርስ ጉሙሩክ በኦን ላይን ለባለንበረቱ ያሳውቃል። እንደየስራ ባህሪያቸው ለዚህም ያደረጀናቸው የሥራ ክፍሎች አሉን። ይህ አንዱ ሎጂስቲክስን የምንደግፍበትና የኑሮ ውድነትን የምናቃልልበት መንገድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እዚህ ጋር በደረቅ ወደብ ለሚመጡ 15 ቀናት በአየር ለሚመጡ ደግሞ 10 ቀናት ብለዋል። ነገር ግን ደንበኞች ንብረታችን እየጠፋ ነው ይላሉ። እነዚህን ነገሮች ለማስቀረት የሔዳችሁበትን ቢገልፁልኝ?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** ጉምሩክ ጋር እቃ አይጠፋም። ምክንያቱም ዕቃው የሚጓጓዘው በአየር ከሆነ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዕቃውን በሰነድ ተረክቦ ያጓጉዛል። በመቀጠል በራሱ መጋዘን ይከታል። አሰራሩ ይሔ ነው። በዚህ መንገድ ላይ ዕቃዎች የሚጠፉ ከሆነ ዕቃውን መክፈል ያለበት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው። በዚህ ዓይነት ተጓጉዞ አየር መንገዱ ለግምሩክ ካስገባ በኋላ ደግሞ በሰነድ ርክክቡ ይፈፀማል።

**አዲስ ዘመን፡- ከተረከባችሁ በኋላ ከግምሩክ ዕቃ አይጠፋም?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** በፍፁም አይጠፋም፤ የምንጠይቅበት ጥብቅ ሥርዓት አለ። የምንመዘግብበት፣ ለባለቤቱ የምናስረክብበት ግልፅ ሥርዓት አለ። በየብስ ተጓጉዞ የሚደርስም ካለ ተመሳሳይ ነው። የኢትዮጵያ ባህር ሎጀስቲክ ያጓጉዛል። በተመሳሳይ መንገድ መጋዘን አስገብቶ እርሱም ያስረክባል።

**አዲስ ዘመን፡- ሌላኛው የኮሚሽኑ ትልቅ ሥራ ኮንትሮባንድን የተመለከተ ነው። በእርሶ አረዳድ መሠረት ኮንትሮባንድ እየጨመረ ነው ወይስ እየቀነሰ? ለምን?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** ኮንትሮባንድ እና ሕገወጥ ንግድ በጣም ፈተና ነው። እንደአገራዊ ትልቅ ተግዳሮት መታየት ያለበት ነው። ወደ ኋላ ሔደን ማየት ጠቃሚ ነው። ከሪፎርሙ በፊት ኮንትሮባንድ ውስጥ ብዙ እጁን ከቶ የሚሰራ ስለነበር ያዝኩ የሚለውም፣ የሚጠቀመውም ይኸው ወገን ስለነበር ወደ መገናኛ ብዙሃን አይወጣም። ከሪፎርሙ በኋላ ኮንትሮባንድ አጀንዳ የሆነበት ትልቁ ሚስጢር አንደኛ ነባር በሽታ ስለነበር፤ ነባሩ በሽታ ወደ መድረክ መጥቷል። በዚህ ምክንያት በፊት ተሸፍነው የኖሩ ኮንትሮባንዲስቶች በግልፅ መጥተዋል። ከዚያ ፍጥጫ እና ግርግር መጣ። ይህን የመጣውን ግርግር ተከትሎ፤ በዚህ አጋጣሚ እንጠቀማለን ያሉ በከፍተኛ ደረጃ መሰማራት ጀመሩ። ዘርፎ እና አስዘርፎ መክበር የተለመደ እንደነበር ይታወሳል። በመሆኑም ግርግር ለሌባ ያመቻል፤ እንደሚባለው በወጪ ንግድ ኮንትሮባንድም ሆነ በገቢ ንግድ ኮንትሮባንድ ላይ በስፋት መሠማራት ጀመሩ።

**አዲስ ዘመን፡- በተለይ በጠረፍ አካባቢዎች በሱዳን፣ በሞያሌ እና በቶጎ ጫሌ፣ ፍተሻዎች ላይ አፋር እና በሌሎችም አካባቢዎች አሁንም ድረስ ያልጠሩ ነገሮች የሉም?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** እመጣበታለሁ። ያለፈውን እንደመነሻ ለመጥቀስ እንጂ ዛሬም ቢሆን ኮንትሮባንድ የአገራችን አንደኛው ጠንቅ ነው። የኢንቨስትመንቱ፣ የንግድ ሥርዓቱ አጠቃላይ ለሕጋዊ ንግድ ሥርዓቱ በጣም ጠንቅ የሆነ ከፍተኛ ተግዳሮት ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ምን እየተሠራ ነው የሚለውን ዓይተን እየጨመረ ነው ወይስ እየቀነሰ ነው? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል። ከ2011 ዓ.ም ጀምረን በጣም በከፍተኛ ደረጃ የፀረ ኮንትሮባንድ ንቅናቄው ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ መጠን እያደገ የመጣበት እና መቆጣጠር የተቻለበት ጊዜ ነው። ይህ በኢትዮጵያ ታሪክ ያለማጋነን ለውጡን ተከትለን በወሰድናቸው የመቆጣጠር እርምጃዎች ከፍተኛ ሥራ ተሠርቷል።

የተቆጠሩ ውጤቶች መጥተዋል። ይህን በመረጃ አስደግፈን ማቅረብ እንችላለን። ለምሳሌ 2011 ላይ ኮሚሽኑ አጠቃላይ ገቢ ወጪ ሕገወጥ ንግድን እና በህጋዊነት ሽፋንም የነበረውን ኮንትሮባንድ የመቆጣጠር አቅሙ 9 ነጥብ8 ቢሊዮን ብር የሚገመቱ ቁሳቁሶችን ለመቆጣጠር ተችሏል።

2012 ዓ.ም ላይ ግን የመቆጣጠር አቅማችን ወደ 26 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ለመቆጣጠር ተችሏል። በ2013 ዓ.ም ደግሞ የመቆጣጠር አቅማችን ወደ 36 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር አድጓል። 2014 ዓ.ም ደግሞ 50 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን፤ 2015 ዓ.ም ላይ በስድስት ወር ውስጥ ብቻ 40 ነጥብ 7 ቢሊዮን መቆጣጠር ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ በሁለት እና በሶስት እጥፍ ያደገ ነው። ኢትዮጵያ በኮንትሮባንድ አደጋ ውስጥ ናት ማለት ነው?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** ይህ ሁለት ጉዳዮችን ያመለክታል። አንደኛው አገሪቷ በገቢም ሆነ በወጪ ኮንትሮባንድ በከፍተኛ ደረጃ የምትፈተን መሆኑን ያሳያል። ሌላው ደግሞ በርትተን ስንሰራ ውጤት እንደምናመጣበት የሚያሳይ ነው። የኮንትሮባንዲስቶቹ ስፋት እና ጉልበት እንዲሁም አደገኝነቱ በዛው ልክ አለ። ስጋቱ እና ተግባሩ ቢኖርም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚሠራው ስራ እያደገ መምጣቱንም የሚያሳይ ነው። ለየብቻ ማየት ይቻላል። ለምሳሌ የገቢ ኮንትሮባንዱን ራሱን አስችለን ማየት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ለየብቻ እንያቸው?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** ከላይ የጠቀስነው ገቢ ኮንትሮባንድ፣ ወጪ ኮንትሮባንድ እና በሕጋዊ ንግድ ሽፋን የሚፈፀመውን አጠቃላይ ነው። ከዚህ ውስጥ የገቢ ኮንትሮባንድን ብቻ ስናይ በ2011 ዓ.ም 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን ሲሆን፤ በ2012 ዓ.ም ደግሞ 2 ነጥብ 14 እንዲሁም በ2014 ዓ.ም 4 ነጥብ 284 ቢሊዮን ነበር። ዘንድሮ በ2015 ዓ.ም በግማሽ ዓመት 4 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የሚገመት ቁሳቁስን መቆጣጠር ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- ይህቺ አገር ወደብ የላትም። ይህን ያህል ኮንትሮባንድ እንዴት ተስፋፋ? ይህ የአገረ መንግሥት ስጋት አይሆንም፤ የእናንተ ትንተና ምንድን ነው?**

**ኮሚሽነር ደበሌ፡-** የጀመርኩትን ልዘርዝር እና ወደዛ እገባለሁ። ወጪ ኮንትሮባንድ ማለትም ከአገሪቱ ወደ ውጪ ከሚላከው ምርት ማግኘት ያለባትን ገቢ በማሳጣት ትርፍ ለማግኘት የሚደረግ ስግብግብነት ነው። ስለዚህ በ2011 ዓ.ም 334 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር የሚገመት ወጪ ዕቃን መያዝ የተቻለ ሲሆን፤ በ2012 ዓ.ም 294 ሚሊዮን ብር የተገመቱ በ2013 ዓ.ም ደግሞ 633 ነጥብ 8 ሚሊዮን

‹‹ዕፅ በአስደንጋጭ ሁኔታ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ኢትዮጵያ ሆይ! “ሣቅሽን ማን ዘረፈው!?”

**የመነሻ ወግ፤**

ከሁለት አሥርተ ዓመታት በፊት ይህ ጸሐፊ በአንድ የውጭ ሀገር በተገኘበት አጋጣሚ መረር ያለ ሞጋች የውስጥ ስሜት አጋጥሞት ነበር:: ያ ክስተት ያጠላው የሀዘን ድባብ ዛሬም ድረስ ደብዝዞ ሊጠፋ አልቻለም:: ሙግቱ አገርሽቶ በትዝታ ለመቆዘም ምክንያት በሆነው በዚያ ጉዳይ መነሻነት ወጋችንን መጀመሩ መልካም ሆኖ የታየኝ በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ የኑሮ ዘይቤ ውስጥ ያ ስሜት የአብዛኛው ሕዝብ የዕለት ተዕለት መለያ መሆኑን በማስተዋሌ ነው:: እነሆ የገጠመኙ ትውስታ::

ጸሐፊው በተገኘበት በዚያ ሀገር ከተቀበሉት ወዳጆቹ መካከል አንደኛው ቤተሰብ ሀገር ቤት በነበሩ ጊዜ በጣሙን ይተዋወቁ ስለነበር ሲገናኙ የተፈጠረው የናፍቆት መግለጫ ስሜት የሚዘነጋ አይደለም:: የቤተሰቡ አባወራ በቀድሞ የእስታትስቲክ መ/ቤት ሠራተኛ የነበረ ሲሆን ባለቤቱም እንዲሁ የተሻለ በሚባል ኃላፊነት ላይ ነበረች:: የዕድል ጉዳይ እንዲሉ ከመጀመሪዎቹ ዙሮች በአንደኛው የዲቪ ሎተሪ እጣ ወጥቶላቸው ከሀገር የወጡት ጋብቻቸውን በፈጸሙ ሰሞን ነበር::

በፍልቅልቅነቷ ሀገር የሚያውቃት ያቺ እህታችን ልዩ መገለጫዋ በዜማ የታጀበ ሣቋና ኩርፊያ የሚባል ነገር ያለማወቋ ነበር:: በወቅቱ ለአንድም ቀን ፊቷ አዝኖና ዳምኖ አይተናል የሚል ሰው ማግኘት አዳጋች ነበር:: ከዚህች እህት ጋር በተገናኘንበት ወቅት ያ ቀድሞ የምትታወቅበት ሣቅና ጨዋታዋ ከእርሷ ዘንድ አልነበረም:: ጨዋታ አድማቂነቷም ፍጹም ሸሽቷት ዝምታ የሚያስቆዝማት ሆኖ መታየቷ በእጅጉ ግራ ያጋባ ነበር::

በዚህ ያልተለመደ ባሕርይዋ የተደነጋገረው ይህ ጸሐፊ “እህቴ ሆይ ምን ሆንሽ? ያ ሣቅሽና ፈገግታሽ ወዴት ሄደ? ምንስ የከፋ ነገር ቢገጥምሽ?” በማለት ደጋግሞ ሲጠይቃት እምባ እየተናነቃት የሰጠችው መልስ፡- “የዚህ ሀገር ኑሮና ሕይወት ሣቄን ዘርፎኝ ሆደ ባሻ ሆኛለሁ:: ፈገግታዬም ጨልሟል…” የንግግሯን ዐረፍተ ነገር ሳትጨርስ ባለቤቷ ፈጠን ብሎ “ሣቄን ተሰረቅሁ! ተዘረፍሁ! የሚሉት ፈሊጥ አላት:: እባክህ እርሷን ተዋትና ወደ ሀገር ቤት ጭውውታችን እንመለስ” ::

“እንደራሷ ሀገር ጣራው እስኪገነጠል ድረስ ካልሣቅሁና ካላሣቅኋችሁ ማለት እዚህ ሀገር አይሠራም:: ሣቅ ካማራትና መንከትከት ካስወደዳት እዚያው የናፈቃት ሀገሯ ትግባ! ወይንም ከባሕሉና ከሕዝቡ አኗኗር ጋር ራሷን አስማምታ ትኑር…” ባልም ግሳጼውንና ቁጣውን አንጠልጥሎ የተወው እንደ መበሳጨት እያለ ነበር::

“ሣቄን ዘረፉኝ! ሣቄን ሰረቁኝ!” ይህ ንግግር ዛሬም ድረስ በፍጹም በውስጤ ማቃጨሉን አላቆመም:: በቀንም በሌትም “ለካስ ሣቅም ይዘረፋል!?” የሚለው ጥያቄ ሕሊናዬን ሠንጎ እንደያዘኝ አስታውሳለሁ:: ይህን መሰሉን የሕመም ስሜት በወቅቱ ለማስታገስ የሞከርኩት የዚያችን ምስኪን እህቴን የንግግር ኃይለ ቃል ተውሼ በብዕሬ ጉልበት መተንፈስ ነበር:: እናም ውስጤ እየተተረማመሰም ቢሆን “ሣቄን መልሱልኝ!?” በሚል ርዕስ አንድ ግጥም ጽፌ አበርክቼላታለሁ::

ግጥሙን በርከት ብለው በተሰበሰቡ የጋራ ወዳጆቻችን ጉባዔ ላይ ቆሜ ባነበብኩበት አጋጣሚም አብዛኞቹ አድማጮቼ ዐይናቸው በእንባ ሲረጥብ አስተውያለሁ:: ዛሬም የተሠረቀው የእህቴ ሣቅ ይመለስላት አይመለስላት እርግጠኛ አይደለሁም:: ያ ፍልቅልቅ ተፈጥሮዋ ተመልሶላት ከሆነ እሰዬው::

ወጤቱን የማውቀው ይህንን ጽሑፍ ልኬላት መልስ ስትሰጠኝ ይሆናል:: እስከዚያው ድረስ ግን

**አንጀታችንን በአንጀታችን ቋጥረን ረሃብን መቋቋም ባሕላችንም ወጋችንም ነው - አላማረርንም:: በጦርነት ተጋድለንና ተቋስለን “በሆድ ይፍጀው” ብሂል የደም ሸማችንን ጠቅልለን ማስቀመጡንም በሚገባ እናውቅበታልን - ‹ግደል ተጋደል› ተለምዷዊ መፈክራችንም አይደል**

“የሣቅ መዘረፉ ክስተት” ኃዘንተኛ በሆነችው ሀገሬም የባሕል ያህል ሥር እየሰደደ ስለሆነ ብንወያይበት አይከፋም በሚል እምነት የሰነበተውን የትዝታዬን ወግ ለማጋራት መልካም መስሎ ታይቶኛል::

**“ኃዘንተኛ እናቴ!”**

ኢትዮጵያ በታሪኳ ውስጥ ከትከት ብላ እየሳቀች የኖረችባቸው ዓመታት የትኞቹ ዘመኖች ይሆኑ? ለዚህ ጥያቄ በቀላሉ መልስ ለመስጠት እንደሚያዳግት አይጠፋኝም:: በወቅት ወለድ ፈተናዎች ብቻም ሳይሆን ሀገሬ የታሪክ ኃዘንተኛ ሆና ለዘመናት እንደኖረችም ይገባኛል::

በየትኛው ዘመን ከትከት እያለች ስቃ እንደነበር የአንተን ምላሽ አስቀድመህ ግልጽ አድርግልን የሚባል ከሆነ ግን የእኔ የአምደኛው መልስ አይ+አዎ (አያዎ Paradox) ይሉት ብጤ ነው:: የአያዎ መልሴን ይበልጥ እንዲያብራራልኝም አንድ ነባር ሀገራዊ “ተረት” ማስታወሱን መርጫለሁ::

“ሰማዩን ካልጨበጥኩ፣ ምድርን ካልጠቀለልሁ በሚል አፍቃሬ ራስነት የሚታወቅ አንድ እብሪተኛ የአካባቢ ሹም አንድ እለት አገልጋዩን ጠርቶ የሚከተለውን ትዕዛዝ አዘዘው ይባላል:: ሩቅ ሀገር ወደምትገኘው እናቴ ዘንድ ሄደህ ጤንነቷን ጠይቀህልኝ ተመለስ:: እናቴ ሞታ ከሆነ መርዶውን በነገርከኝ ቅጽበት አንተም የእርሷ እድል ይገጥምሃል:: በጤንነት አግኝተሃት መልካም ዜና የምታመጣልኝ ከሆነ ግን እሾምሃለሁ፣ እሸልምሃለሁ:: ምርጫው የራስህ ነው::”

“ምስኪኑ አገልጋይ የጨካኙን አስተዳዳሪውን የአደራ መልዕክት ተቀብሎ ወደ ተላከበት የእናቱ ሀገር ገሠገሠ ይባላል:: ከተባለው ቀዬ ብቅ ሲልም የሹሙ እናት ሞተው የቀበሌው ሕዝብ እዬዬውን ሲያቀልጠው ይደርሳል:: በኃዘኑ ቤት እንደምንም እስከ ሰልሥቱ ከሰነባበተ በኋላ የጎፈሬውን ግማሽ ተላጭቶ፣ ግማሹን እንደነበረ አጎፍሮ ወደ ጌታው ቤት ተመለሰ:: ጌቶችም መምጣቱን እንደ ሰሙ ‹እናቴን ደህና አገኘሃት?› ብለው ሲጠይቁት ወደ ተላጨው ጎፈሬው አመለከታቸው::

‹ወዬው እምዬ ሞተች ማለት ነው?” ብለው እሪታቸውን ሲያቀልጡ ‹ቢሞቱ ኖሮ ጎፈሬዬን አጎፍራለሁ?› በማለት ያልተላጨውን የጎፈሬውን ግማሽ ከመከም በጣቶቹ ጠቆማቸው:: ሞታለች? አልሞተችም? እያሉ መሚገታቸውን ለጊዜው አልገፋበትም:: የሚሻለው “አፌን በዳቦ አብሱ” በማለት መረርና ጠነን ወዳለው ሀገራዊ ጉዳያችን መመለሱ ይሻል ይመስለናል:: “ኢትዮጵያ በታሪኳ ውስጥ ስቃ ታውቃለች? ወይንስ አታውቅም?” ለሚለው ጉንጭ አልፋ መሚገቻ ይህ የተረት ትረካ መልሱን የሰጠ ይመስለናል::

**“ሣቅ ብርቁ ሀገሬ!”**

“ያ ትውልድ” እየተባሉ ከሚታወሱት የሀገራችን አፍቃሬ ለውጥና ሞገደኛ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የኮሌጅ ተማሪዎች መካከል ገጣሚ ዮሐንስ አድማሱ አንዱ ነበር:: ይህ ትንታግ ብዕረኛ የነበረበትን ፊውዳላዊ ዘመን እንደምን በግጥሙ ያብጠለጥል እንደነበር በብዙዎች ዘንድ ይታወሳል:: በተለይም “ኃዘንተኛ እናቴ” በሚል ርዕስ ጽፎ ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው በተገኙበት የኮሌጅ ቀን ላይ በ1954 ዓ.ም ካነበው ረጅም ግጥሞቹ መካከል ጥቂት ስንኞችን ተውሰን እንደሚከተለው እናስታውሳለን::

**“ኃዘንተኛ እናቴ ኃዘንሽ ቢበዛ፣**
**መልክሽ ጠቆረብኝ ሆነብኝ ቀዛዛ::**
**ምንም ቤትሽ ቢፈርስ ኑሮሽ በደረባ፣**
**እግርሽ ቢሰነከል ብትሆኚ ሰለባ፣**
**ዳግመኛ እንድትመጪ ይታየኛል እኔ፣**
**ለልቤ ደስታ ሐሴት ለዘመኔ::**
**ትካዜሽ ወጨፎ ሰቀቀን ጭፈና፣**
**ሸረጠጠው ልቤን አደረገው መና::**
**ኃዘንተኛ እናቴ የመጣውን ቀንበር እኔም ልሸከም፣**
**ልረስ ልቆፍረው በተለምሽው ትልም::**
**ፈንታዬን ተወጣሁ ፍጆታው ለሌላ፣**
**የትልሙን ማቃኛ ይፍጠር ሌላ መላ::”**

ይህ ግጥም ከሺህ ቃላት በተሻለ ትናንትን ብቻ ሳይሆን ዛሬንም በአግባቡ የሚገልጽ ይመስለኛል:: ሀገሬ ሣቅ ርቋት፣ ኃዘን አጥልቶባት መኖርን የባሕል ያህል በአሜንታ ተቀብላ ስለመኖሯ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሀገር የሚያውቀው ነው:: “ሣቅ ብርቋ፣ ኃዘን ውርሷ” ሆኖ እስከ መቼ ትኖራለች የሚለውን ጥያቄ እንደ ሕዝብ መጠየቅ ጊዜው የሚፈቅድ ይመስለናል::

የተዳፈሯትን ወራሪዎች ድል በመታች ማግሥት የተሰዉባትን ልጆቿን እርም አውጥታ ሳትጨርስና የኃዘን ጨርቋን ከመለወጧ አስቀድሞ ሌላ መልክ ብዙ አበሳዎችን ስትጋፈጥ ስለመኖሯ በዝርዝር እንተርክ ብንል ሰማዩ ብራና፤ ዓባይ ወንዛችንም ቀለም ቢሆን ተጽፎ ስለመጠናቀቁ እርግጠኛ ለመሆን ያዳግታል::

“ደስተኛና ሣቂታ ብቻ ሳይሆኑ የተደላደለ ኑሮ ያላቸው ሀገራት” በሚል ርዕስ ከአንድ ዓመት በፊት በተጠና ዓለም አቀፍ ጥናት መሠረት የክብር ደረጃውን የተጎናጸፉት አብዛኞቹ ሀገራት ስካንዲኔቪያን በመባል የሚታወቁት እንደ ፊንላድ፣ ዴንማርክ፣ ኖርዌይ፣ ስዊድን ወዘተ. የመሳሰሉት ሀገራት ናቸው:: የእኛይቱ “ኃዘንተኛ አደይ” የተሸቀነጠረችው ወደ 130ኛ ደረጃ ነበር:: ዛሬ ቢሆን ምናልባትም ወደ ኋላ አፈግፍጋ ከመጨረሻዎቹ የዓለም ሀገራት ዋነኛዋ ሳትሆን አትቀርም::

የኢትዮጵያ የመከራ ሱናሚ መቼ እንደሚሰክን ለመተንበይ የሚቻል አይመስልም:: ፈውስ አልባ የሆነው በሽተኛው ፖለቲካችን የሀገራችንን ሣቅ ነጥቆ “ኃዘንተኛ” ካደረጋት ዓመታት ነጉደዋል:: ይህም ያነሳት ይመስል በየጊዜው መልኩን እየለዋወጠ ፈገግታ አልባ የሚያደርጋት መከራ መቼ ከፍጻሜ እንደሚደርስም ለማወቅም ሆነ ለመተንበይ እንዳዳገተን እነሆ ዘመን ጠብቶ ዘመን እየመሸ ነው::

ጸሎታችንና ጾማችን፣ እርቅና መሸማገላችን፣ ይቅር መባባላችንና መወቃቀሳችን ስለምን ፍሬ አፍርቶ ከመከራ እንደማያሳርፈን እንደእንቆቅልሽ ከመሆንም አልፎ የባሕል ያሕል ተጣብቶን የኑሯችን አንዱ ክፍል እስከ መሆን ደርሷል::

ፖለቲካውን ስናስታምም ኢኮኖሚው ጤና አጥቶ አልጋ ላይ ይውላል:: ማኅበራዊ መስተጋብራችንን ያጠበቅን ሲመስለን የኅጠኝነትና የብሔር ልክፍት በየጊዜው እያገረሸ ያጥወለውለናል:: ወደየቤተ እምነቶቻችን ፊጥነን እየሮጥን ፈጣሪን የሙጥኝ እንዳንል የመሰናክሎቻችን አበዛዝ የትየለሌ ሆኖ ግራ ተጋብተናል::

ሕጉን በሕግ አምላክ ብንለው አልሰማ ብሎናል:: ጉልበተኞችንም በጉልበት አምላክ እያልን ብንማጸናቸው እብሪታቸውን አጠናከሩ እንጂ ተማጽኗችን ሊያራራቸው አልቻለም:: በወንጌል/በቁርአን አምላክ እያልን ሰባት ጊዜ ሰባ ሱባዔ ብንገባም ሰሚ አምላክም ሆነ አሰሚ አማላጅ አለሁ ሊለን አልቻለም:: ስለዚህ ኢትዮጵያ ሣቋ ተነጥቆ ፈገግታዋ ጨልሞ “የኃዘን ከል እንደለበሰች” ብትኖር መች ይፈረድባታል?

አንጀታችንን በአንጀታችን ቋጥረን ረሃብን መቋቋም ባሕላችንም ወጋችንም ነው - አላማረርንም:: በጦርነት ተጋድለንና ተቋስለን “በሆድ ይፍጀው” ብሂል የደም ሸማችንን ጠቅልለን ማስቀመጡንም በሚገባ እናውቅበታልን - ‹ግደል ተጋደል› ተለምዷዊ መፈክራችንም አይደል:: ፖለቲካና ዘመን አመጣሽ አይዲዮሎጂ ሲያመሳቅለንም በጎሪጥ እርስ በእርስ እየተጎሸማመጥን መተላለፍን ተክነንበታል - ደም ተቃብተንም ቢሆን አብረን መኖርንም በሚገባ እናውቅበታለን!

ይሄ ሁሉ ሀገራዊ ወፈፍታ አልበቃ ብሎን እነሆ ሌላ አሳርና መከራ ዝናብ እንዳረገዘ ደመና እያንጃበበ ለስቅቅ ዳርጎ አሸማቆናል:: ይህ ከቤተ እምነቶቻችን ጎራ አፈትልኮ የሚወጣው መብረቃዊ ሞገድ በጊዜ ታክሞ ካልዳነ በስተቀር ምን ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ለመገመት እንኳን የሚያዳግት ሆኖብናል:: “ለእኔ እናት ምን በጃት፣ ያም አፈር ያም ድንጋይ ያም ኮረት ጫነባት” ያለችው አልቃሽ እውነት ብላለች::

ቀደም ሲል የጠቀስነው ባለቅኔ ዮሐንስ አድማሱ “እስኪ ተጠየቁ” በሚል ርዕስ በ1954 ዓ.ም ከጻፈው የኮሌጅ ቀን ሌላው ግጥሙ ውስጥ በሚከተሉት ጥቂት ስንኞች ሃሳባችንን እናሳርጋለን::

**“ይዘልቃል ወይ ከቶ በንዲህ ዓይነት ስልት፣**
**ወጋግራውን ሁሉ ምሶሶውን ሁሉ ቁንቁን ጨርሶት::**
**እንዲህ እንደሆነ ቤቱ በውነት፤ ባለም መቃብር፣**
**ማገሩ ሁሉ አልቆ ቤቱ ሆኖ አፈር፤**
**ግድግዳ ብቻዋን ቤት አትሆንም ሰልታ፣**
**በግድ የለሽ ሥራ አለማገር ቀርታ::**
**ወደፊትም ደግሞ ታስቡ እንደሆነ ትልቅ የቤት ሥራ፣**
**ግድግዳና ጣሪያው እንዲያምር በተራ፣**
**አለማገር ሆኖ እንዳይፈርስ አደራ::”**

ነብየ እግዚአብሔር ኤርሚያስ ቢቸግረውና ግራ ቢገባው የሚከተለውን ጸሎት ወደ ፀባኦት ያደረሰው እንደሚከተለው በመቃተት ነበር:: “አቤቱ! የሆነብንን አስብ፤ተመልከት፣ ስድባችንንም እይ::…የሽማግሌዎች ፊት አልታፈረም:: …የልባችን ደስታ ቀርቷል፤ ዘፈናችን ወደ ልቅሶ ተለውጧል:: አክሊል ከራሳችን ወድቋል:: ስለዚህ ልባችን ታሟል:: ስለዚህም ነገር ዓይናችን ፈዝዟል:: ስለ ምን ለዘላለም ትረሳናለህ? ስለ ምንስ ለረጂም ዘመን ትተወናለህ? ወደ አንተ መልሰን እኛም እንመለሳለን” (ሰቆቃወ ኤርምያስ ምዕ. 5):: አሜን! የኢትዮጵያ ሣቅ ከተዘረፈበት አድራሻ እንደ ሀገራዊ ቅርሶቻችን ተመልሶ ለማየት ፈጣሪ ይርዳን::

**ሰላም ለሀገሬ! በጎ ፈቃድም ለዜጎች::**

# ከዋጋው ትመናው በላይ ቁጥጥርና ክትትል የሚያሻው የሲሚንቶ ገበያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**



መንግሥት ለግንባታው ዘርፍ ቁልፍ የሆነውን የሲሚንቶ እጥረት ለመቅረፍ ሲል በርካታ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየናረ የመጣውን የሲሚንቶ ዋጋ የተጋነነ ዋጋ እንዳይኖረውና ገበያውን ለማረጋጋት በሚል አማራጮችን በማፈላለግና አዳዲስ መመሪያዎችን በማውጣት ሲሠራ መቆየቱ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት አላስቻለውም።

እንደሚታወቀው መንግሥት የሲሚንቶ ዋጋን ወስኖ በመንግሥት ቁጥጥር ውስጥ በማድረግ ገበያውን ለማረጋጋት ያደረገው ጥረት ባለመሳካቱ ምክንያት ሲሚንቶን ከእጁ በማውጣት እንደቀደመው ጊዜ ሁሉ ሲሚንቶ በነጻ የንግድ ሥርዓት እንዲመራ መወሰኑ ይታወሳል። ይህን ውሳኔ ተከትሎም በተወሰነ መጠን እጥረት ቢኖርም ሲሚንቶ በችርቻሮ መሸጫ ሱቆች መታየት እንደጀመረና የተሻለ ስርጭት እየታየበት እንደሆነ መታዘብ ተችሏል።

ይህን መነሻ በማድረግም በየጊዜው የሚታየውን የሲሚንቶ ገበያ አለመረጋጋት በማስቀረት ብሎም የተረጋጋ ገበያ እንዲፈጠር በሚል ባሳለፍነው ሳምንት መጨረሻ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ ምክክር አድርጓል። በምክክሩም የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ ተቆርጦለታል። የተወሰነው የመሸጫ ዋጋም ከጥር 22 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚሆን ተወስኗል።

በዕለቱ የተገኙት የሲሚንቶ አምራቾች ቦርድ ሰብሳቢ አቶ አዱኛ በቀለ የሲሚንቶ ዋጋ ቁጥጥርና ስርጭትን አስመልክተው እንደገለጹት፤ በተያዘው ሳምንት ሲሚንቶ በተወሰነለትና አዲስ በተቆረጠለት ዋጋ የማሰራጨቱና የማከፋፈሉ ተግባር ይከናወናል። በዚሁ መሠረትም ለመንግሥት ፕሮጀክቶች፣ ለግል ቤት አልሚዎች (ሪልስቴት) ኮንክሪት የማደባለቅ (ሚክስ)የሚሠሩ ድርጅቶችም እንዲሁ ሲሚንቶ በቀጥታ ከፋብሪካው ማግኘት የሚችሉበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል።

በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ የሲሚንቶ ፍላጎት ከ60 በመቶ በላይ በመሆኑ የመሸጫ ዋጋ ተወስኗል። በዚህ ወቅት አዲስ አበባ ከተማ ላይ ያለው የሲሚንቶ ችርቻሮ ዋጋ ዳንጎቴ ሲሚንቶ በኩንታል 1106 ብር ከ85 ሳንቲም፣ ደርባ ሲሚንቶ 1067 ብር ከ33 ሳንቲም፣ ሙገር ሲሚንቶ 1016 ብር ከ52 ሳንቲም፣ ኩዩ ሲሚንቶ 1065 ብር፣ ካፒታል ሲሚንቶ 1026 ብር ከ35 ሳንቲም መሆኑን መሆኑን የጠቆሙት አዱኛ፣የሁሉም ሲሚንቶ አምራች ድርጅቶች የመሸጫ ዋጋ ከ1200 ብር በታች እንዲሆን እና እያንዳንዱ የማኅበረሰብ ክፍል በተወሰነው ዋጋ ሲሚንቶ ማግኘት የሚያችልበት አሠራር መዘርጋቱን አመልክተዋል። ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ የክልልና የዞን ከተሞች ጋርም ተደራሽ ለመሆን እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

እንደ አቶ አዱኛ ማብራሪያ የሲሚንቶ ምርት እጥረትና የገበያ አለመረጋጋትን ለመከላከል የተለያዩ አማራጮች ሲወሰዱ ቆይተዋል። በዚሁ መሠረትም የሲሚንቶ እንደቀደመው ጊዜ ሁሉ በነጻ ገበያ እንዲመራ በመንግሥት መፍቀዱ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ከጥር 22 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ሲሚንቶ በተተመነለት ዋጋ ለገበያ ይቀርባል። ፋብሪካዎች የማጓጓዣ ወጭን ጨምሮ ያለባቸው ወጪ የተለያየ በመሆኑ ገበያ ላይም የተለያየ ዋጋ ይዘው ነው የሚቀርቡት።

ሲሚንቶ አምራች ፋብሪካዎች ሲሚንቶ እንዲሸጡ የተፈቀደው ትክክለኛ የንግድ ፈቃድ ላለው፣ የሽያጭ ደረሰኝ መቁረጥ ለሚችልና ቋሚ አድራሻ ላለው ነጋዴ ብቻ ነው። በገበያው ሰንሰለት ውስጥ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎችም ይሳተፋሉ። አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች በገቡት የውል ስምምነት መሠረት ምርቱን ለሸማች ያደርሳሉ። ፋብሪካዎች የሚያቀርቡበት እና የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን ለሸማቹ በግልጽ የማሳወቅ ግዴታም ተጥሎባቸዋል። የመሸጫ ዋጋው ሸማቹ ማየት በሚችልበትና ግልጽ በሆነ ቦታ መለጠፍ ይኖርበታል።

መንግሥት የስርጭቱን ሂደት አስመልክቶ ያወጣውን መመሪያ ያልተገበሩ መኖራቸውን ያስታወሱት አቶ አዱኛ፤ድርጊቱ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመገንዘብ ወደ መደበኛ የገበያ ሥርዓት እንዲመለስ በመደረጉ በሲሚንቶ ግብይት ላይ አሁን እየታየ ያለውን ውጤት ማምጣት ተችሏል ብለዋል። በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር ሙሉ ለሙሉ መቅረፍ የሚቻለው አቅርቦትና ፍላጎት ማጣጣም ሲቻል እንደሆነ ጠቁመዋል። በዚህ ረገድም የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ እንደሆነ አንስተዋል። ወደ ሥራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ያሉ አዳዲስ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች እና የማስፋፊያ ሥራ ውስጥ የገቡ ጥቂት የማይባሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ማምረት ሲጀምሩ በምርት አቅርቦትና በዋጋ የሚስተዋለው ችግር ይቀንሰዋል የሚል ተስፋቸውን ገልጸዋል።

‹‹ከዚህ ቀደም የነበረው የሲሚንቶ ዋጋ የተጋነነ ከመሆኑም ባለፈ የምርቱ አለመገኘት ፈታኝ የነበረ ሲሆን፤ ነጋዴው አሁን በተቀመጠው የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ሲሚንቶን ለማኅበረሰቡ የሚያቀርብ ይሆናል። ለተግባራዊነቱም የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ቁጥጥር ያደርጋል›› ያሉት አቶ አዱኛ ከመንግሥት በተጨማሪ በዋናነት ፋብሪካዎችም ሆኑ አከፋፋዮች እንዲሁም ቸርቻሪዎች የየራሳቸው ኃላፊነት አለባቸው ብለዋል።

ከዚህ ቀደም ሲሚንቶን በከፍተኛ መጠን ይፈልጉ የነበሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ለአብነትም በቤት ልማት ላይ የተሠማሩ በሲሚንቶ እጥረት ምክንያት ሥራ አቁመው እንደነበር ያስታወሱት አቶ አዱኛ፤ አሁን ላይ በዘርፉ በተደረገው ማሻሻያና የዋጋ ትመና መሠረት ግዙፍ ፕሮጀክቶችና ሌሎችም ሥራ ለመሥራት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰው የነበሩ የግብዓቱ ተጠቃሚዎች በቀጥታ ከፋብሪካ ሲሚንቶ መግዛት የሚችሉበት ሁኔታ እንደተፈጠረላቸው አስረድተዋል።

የሲሚንቶ ገበያን ለማረጋጋትና ጤናማ የሆነ የግብይት ሥርዓት ለመፍጠር በሚል “በሲሚንቶ አምራቾች ማኅበር በኩል ይፋ የተደረገው የሲሚንቶ ችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ውስጥ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ድርሻ ምን እንደሆነና ምን ሊሠሩ እንዳቀዱ በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ለሆኑት ለወይዘሮ ቁምነገር እውነቱ ጥያቄ አቅርበንላቸው በሰጡት ምላሽ፤የሲሚንቶ ገበያን አስመልክቶ ከሲሚንቶ አምራቾች ጋር በጋራ በመሆን ወቅታዊ መግለጫ የተሰጠ ሲሆን፣አዲስ በተሻሻለው 940/2015 መመሪያ መሠረት የሲሚንቶ ዋጋ በአምራቹ አንደበት እንዲነገርና አጠቃላይ ያለውን የሲሚንቶ ዋጋ ለማኅበረሰቡ ይፋ እንዲሆን ተደርጓል።

ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሕግ በተሰጠው ስልጣን፣ተግባርና ኃላፊነት መሠረት አንደኛው የሲሚንቶ ምርት አቅርቦትን መነሻ ያደረገ እንደ አስፈላጊነቱ የግብይትና የስርጭት አሠራር ሥርዓትን መዘርጋት ነው። ሆኖም በቅርቡ የወጣውና ወደ ሥራ የገባው አዲሱ መመሪያ ለአሠራር ምቹ ባይሆን እንኳን ወደፊት የማሻሻል፣ የመቀየርና ሌላ የተሻለ አሠራር የመዘርጋት ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አዲስ የአሠራር ሥርዓትን ከመዘርጋት ባሻገር አፈጻጸሙን ይከታተላል። የሚከታተል በተለይም በወጣው መመሪያ መሠረት በትክክል ተፈጻሚ መሆኑን ያረጋግጣል። በተጨማሪም የፋብሪካ መጋዘን የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ መነሻ በማድረግ የጅምላና የችርቻሮ ዋጋ ጣራውን ማውጣቱን መከታተል ሌላኛው ተግባሩ ነው። ይህንንም ተግብሯል።

በዚህ መሠረትም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአሁን ወቅት የሲሚንቶ ምርት አፈጻጸም ስርጭትና የመሸጫ ዋጋ መረጃዎችን በመከታተል ቁጥጥር ያደርጋል። የክትትልና የግምገማ ሥርዓቱንም እንዲሁ በመዘርጋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይፈታል። የመፍትሔ ሃሳቦችንም በማምጣት መፍትሔ የመስጠት ሥራም ይሠራል። ይህ መመሪያ ከተዘረጋ በኋላም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በዚሁ ሳምንት ከሰኞ ጥር 22 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሥራ የገባ ሲሆን፤ የሲሚንቶ ገበያው በተቀመጠው መመሪያ መሠረትና በተቆረጠለት የዋጋ ተመን እየተሸጠ ነው ወይ የሚለውን ክትትል እያደረገ ይገኛል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እያደረገ ባለው ክትትልና ቁጥጥርም አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች የተለያዩ ምክንያቶች እያነሱ እንደሆነ የገለጹት ወይዘሮ ቁምነገር፤ ለአብነትም የመሸጫ ደረሰኝ ሕትመት አለመድረስና የቅደም ተከተል ችግር እና ተያያዥ ችግሮች መኖራቸውን እያነሱ እንደሆነ ተናግረዋል። ይሁንና መመሪያው ከወጣ ገና ሳምንት ያልሞላ ጊዜ በመሆኑ በቀጣይ እነዚህ ችግሮች ተፈተው ሲሚንቶ ያለምንም ችግር በተወሰነለት ዋጋ ሸማቹ ጋር ይደርሳል የሚል ዕምነት ያላቸው መሆኑንና መመሪያው ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮም ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ መሆኑን ነው ያስረዱት። ለክትትልና ቁጥጥሩ የተቋቋመ ግብረ ኃይል መኖሩን በማስታወስም ግብረ ኃይሉ ወደ ሥራ የሚገባ መሆኑን ተናግረዋል።

ክትትልና ቁጥጥሩን በተመለከተ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን ይቆጣጠራል። ግብረ ኃይሉም እንዲሁ በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በኩል ከተለያዩ አካላት ጋር በመሆንም ቁጥጥሩን የሚያደርግ ይሆናል፤ የሚሉት ወይዘሮ ቁምነገር፤ እንደ አዲስ አበባ ከተማ በዋናነት የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የሚከታተለውና የሚቆጣጠረው ቢሆንም ቁጥጥሩን ለማጥበቅ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ይቆጣጠራል ብለዋል። ክልሎችን በሚመለከትም በየራሳቸው የንግድና የገበያ ልማት ቢሮዎች እንዲቆጣጠሩ አዲሱ መመሪያ የሚያዛቸው እንደሆነ ነው የተናገሩት።

አስፈላጊውን እና ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ ካልተቻለ መመሪያ ማውጣቱ ብቻ ምንም ፋይዳ የሌለው እንደሆነ ያነሱት ወይዘሮ ቁምነገር፤ ገበያው ላይ ያለውን ሁኔታ በአካል በመዘዋወር በገበያው ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል ብለዋል። በዚህም በደረሰኝና በትክክለኛው በተተመነው ዋጋ ስለመሸጡ ያረጋግጣል። ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ካልተቻለ ግን ትርጉም የሌለው ሥራ ከመሆን ባለፈ እንደገና ወደ ነበረበት ዋጋ የሚመለስ በመሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋል ብለዋል።

ቸርቻሪዎች ከፋብሪካው በር ሲረከቡ የገቡት ግዴታ ስለመኖሩ በማስታወስም በግልጽ የተቀመጠላቸውን የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በመሸጫ ሱቆቻቸው በሚታይ መልኩ ለሸማቹ እያሳዩ መሸጥ እንዳለባቸው ተናግረዋል። ሲሸጡም በደረሰኝ መሆን እንዳለበትና የተሟላ መረጃ በመያዝ ጤናማ በሆነ የግብይት ሥርዓት እንዲመሩ ነው ያሳሰቡት። በመጨረሻም የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ባለሙያዎችን ጨምሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ዕለት ተዕለት ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ መሆኑን አመላክተዋል።የሲሚንቶ ገበያን በዋጋ በማሻሻልና ስርጭቱንም ተደራሽ ለማድረግ በተጀመረው የተጠናከረ ሥራ ውጤት ይጠበቃል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

# ተማሪዎችን የሚጎዱ አላዋቂ ልማዶቻችን

ዋስልኝ አየለ

የዚህ ሳምንት አንዱ ሀገራዊ አጀንዳ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀገር አቀፍ የፈተና ውጤት ነበር:: ከዚህ በፊት ከነበሩት ዓመታት አንፃር ብዙ ተማሪ ዝቅተኛ ውጤት ያመጣበት ዓመት ነው:: ከ50 በመቶ በላይ ያመጡት 3.3 በመቶ ተማሪዎች ብቻ ናቸው::

በነገራችን ላይ የዘንድሮ የትምህርት ሚኒስቴር ዝርዝር መግለጫ ለብዙ ፖሊሲዎች ግብዓት የሚወጣው ነው:: በፆታ፣ በአካባቢ፣ በትምህርት ቤቶች አይነት፣ በትምህርት መስኮች አይነት፣ በከተማና ገጠር.... በአጠቃላይ በየዘርፉ ምን ይመስል እንደነበር ዝርዝር መግለጫ ሰጥቷል:: ራሳቸው የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንደገለጹት፤ በየዘርፉ ያሉ አካላት «ለምን ሆነ?» የሚለውን ወስደው ሊሰሩበት ይገባል::

የኔ ትዝብት ግን ወዲህ ነው:: የፈተናውን አኃዛዊ መረጃዎች ለባለሙያዎች እንተወውና ተማሪዎችን የሚጎዱ አላዋቂ ልማዶቻችንን ግን እንታዘብ::

ከፈተናው በፊት አንድ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ለተማሪ ወላጆች የጻፈው ነው የተባለ ደብዳቤ በማኅበራዊ የትስስር ገፆች ላይ ሲዘዋወር አገኘሁት:: ደብዳቤውን ቃል በቃል እንደሚከተለው እናስነብባችሁ::

«... ወድ ቤተሰቦች!

የልጆቻችሁ ፈተና በቅርቡ ይጀምራል:: የልጆችዎ ፈተና ጉዳይ እንዳስጨነቀዎ ይገባናል::

ነገር ግን፣ እባክዎን ይህን ያስታውሱ::

ለፈተና ከሚቀመጡት ተማሪዎች መካከል በሂሳብ መራቀቅ የማይጠበቅበት አርቲስት ይኖራል:: ስለታሪክ እና ሥነጽሑፍ ግድ የማይሰጠው የነገ ሥራ ፈጣሪም አለ:: የኬሚስትሪ ውጤቱ ከፍ አለ ዝቅ አለ በሕይወቱ ላይ ለውጥ የማያመጣበት ሙዚቀኛም ከተማሪዎች መካከል አለ::

ከፊዚክስ ይልቅ የአካል ብቃቱ ጉዳይ ወሳኝ የሆነበት አትሌትም ይኖራል::

ስለዚህም ልጅዎ በፈተና ከፍተኛ ውጤት ካመጣ ጥሩ! ዝቅተኛ ውጤት ካመጣ ግን እባክዎን በራስ መተማመኑን እና ክብሩን አይንጠቁት:: ምንም ማለት አይደለም በሏቸው ይልቅ!

ከትምህርት ቤት ፈተና ለላቀ ታላቅ ጉዳይ ወደዚህ ዓለም እንደመጡ ንገሯቸው:: የትኛውንም ውጤት ቢያመጡ እንደምትወዷቸው፤ ዝቅተኛ ውጤት አመጡ ብላችሁ እንደማትፈርዱባቸው ንሯቸው::

አዎን! እባክዎን ይሄን ያድርጉ ... አንድ ፈተና ወይም አነስተኛ ውጤት ሕልምና በራስ መተማመናቸውን፣ ክህሎታቸውን እንዲያሳጣቸው አታድርጉ::

እናም እባክዎን ... ልጆችዎ ገና ለገና ዶክተር እና ኢንጂነር ካልሆኑ ደስተኛ አይሆኑም ብላችሁ አታስቡ!

ከሞቀ ሰላምታ ጋር...»

ይላል ደብዳቤው:: ይህን ደብዳቤ ሳነብ በቀጥታ በአካባቢያችን ይደረጉ የነበሩ ልማዶች ናቸው ትዝ ያሉኝ:: አሁንም የ12ኛ ክፍል ውጤት መለቀቅን አስመልክቶ የሚሰሩ ቀልዶችና ተስፋ አስቆራጭ መልዕክቶች ናቸው የታዩኝ::

በተማረውም ይሁን ባልተማረው ማኅበረሰባችን ውስጥ ያለው አስተሳሰብ ለዕውቀት የተዛባ ቦታ አለው:: ልማዳችን በተለይም ለተሰጥዖ ቦታ የለውም:: አንድ ተማሪ ጎበዝ ነው የሚባለው ሒሳብ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ፣ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ... ትምህርቶችን ጎበዝ ከሆነ ብቻ ነው::

በተለይ የእጅ ሙያ (ሥዕልና ቅርጻቅርጽ)፣ የድምጽ ሙያ፣ የትወና ብቃት፣ የአካል ብቃት(ስፖርት)፣ የአስቂኝነት ተሰጥዖ፣ ወይም ሌላ ለየት ያለ ችሎታ እንደ ብቃት አይታዩም:: እንዲያውም በተቃራኒው የቦዘኔነት ምልክት ተደርገው ነው የሚታዩ:: እውቀት ማለት እነዚያ የትምህርት አይነት ተብለው በክፍለ ጊዜ ተከፋፍሎ የሚሰጡት ብቻ ናቸው::

አዎ! እንደ ፊዚክስ፣ ሒሳብና ኬሚስትሪ የመሳሰሉ ትምህርቶች ዓለምን እዚህ የረቀቀ ቴክኖሎጂ ላይ ያደረሱ ወሳኝ መሠረታዊ የሳይንስ ትምህርቶች ናቸው:: ዳሩ ግን ሕይወት ማለት ደግሞ በእነዚህ ትምህርቶች ጎበዝ መሆን ማለት ብቻ አይደለም::

የአገራችንንም ሆነ የዓለምን ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎችን ማየት በቂ ምስክር ነው:: ከፊዚክስ ተራቃቂው አልበርት አንስታይን ያላነሰ የእግር ኳስ ኮከቡ ሊዮኔል ሜሲ ዝነኛ ነው፣ ተወዳጅ ነው፣ ሀብታም ነው:: ዘፋኙ ማይክል ጃክሰን ከሳይንስ ሊቁ ስቴቨን ሀውኪንግ በላይ የዓለም መነጋገሪያ ነበር::

ታሪካቸውን በቅርበት የምናውቃቸው በየተሠማሩበት ዘርፍ ጀግና የሆኑ የሀገራችንን ዝነኞችም ማየት እንችላለን:: ዘፋኞቹ ጥላሁን ገሠሠ ወይም ቴዲ አፍሮ ዝነኛ እና ተወዳጅ የሆኑት በፊዚክስ ወይም ኬሚስትሪ አይደለም:: የተሰጣቸውን ተሰጥዖ ለተገቢው ዓላማ ስላዋሉት ነው:: እነ ኃይሌ ገብረሥላሴና ቀነኒሳ በቀለ «ጀግና» ተብለው የሀገር ባለውለታ የሆኑት በታሪክ ጥናትና ምርምር ወይም በሒሳብ ሊቅነት አይደለም:: የተሰጣቸውን ተሰጥዖ በተገቢው ዓላማ ስላዋሉት ነው::

እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ሀገርንም ጠቅመዋል ማለት ነው:: የፈጠሯቸው የሥራ ዕድሎች ለሕዝብ ጠቅመዋል ማለት ነው::

አዎ! ሀገራችን የሳይንስ ተመራማሪዎች ያስፈልጓታል:: የአንዲት ሀገር ዕድገት የሚለካው በሳይንስ ዕድገት ነው:: ይህ የሚሆነው ግን በትንቅንቅ ሳይሆን በችሎታ ነው:: የሀገሪቱ ተማሪ በሙሉ የሳይንስ ተመራማሪ ሊሆንልን አይችልም:: ስለዚህ ያለውን የግል ተሰጥዖ እንዲጠቀምበት ዕድል መስጠት አለብን ማለት ነው:: ማሸማቀቅና ምንም የማይጠቅም እንደሆነ መናገር ሞራሉን ይነካል:: የተሰጥዖ ሥራዎች ደግሞ ሞራል የሚፈልጉ ናቸው::

ሌላው የተዛባው አመለካከታችን ብዙ የእጅ ሥራ ውጤት የሆኑ የዕደ ጥበብ ሥራዎች እንደ ሳይንስ የማይታዩ መሆኑ ነው:: አፈርን አቡክተው፣ ከጭቃ ጠፍጥፈው የሸክላ ሥራዎችን የሚሠሩ እናቶቻችን እንደ ሳይንስ ተመራማሪ አይታዩም:: የሳይንስ ውጤት የሚባለው ፈረንጅ የሠራው ሲሆን ብቻ ነው::

እነዚያ ከአገልግሎታቸው በተጨማሪ ለዓይን እንኳን የሚማርኩ የጅማ የእንጨት ውጤቶች እንደ ሳይንስ ሥራ አይታዩም:: ሸክላ፣ የጥጥ ፈትል እና የእንጨት ሥራዎች «ባለ እጅ» እየተባሉ እንደኋላቀር ይታያሉ፤ ይሄ የአስተሳሰባችን ኋላቀርነት እንጂ የረቀቁ ሳይንሶች ናቸው::

ሰሞኑን ይፋ የሆነው የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት የተፈተኑባቸውን የትምህርት አይነቶች ውጤት ብቻ ነው የሚገልጽ:: በእነዚያ ሰባት የትምህርት አይነቶች ውስጥ፤ ሙዚቃ የለም፣ አትሌቲክስ ወይም እግር ኳስ የለም፣ ሥዕል የለም፣ የአገራችን የዕደ ጥበብ ሥራዎች የሉም:: ስለዚህ አንድ ተማሪ በእነዚያ ፈተናዎች ወደቀ ማለት ምንም ችሎታ የለውም ማለት አይደለም::

እስኪ ልብ እንበል! ጅማ በእንጨት ሥራ ላይ የተሠማራ አንድ ወጣት፣ ወይም ሽሮ ሜዳ በሽመና ሥራ ላይ የተሰማራ አንድ ሸማኔ፣ 4 ነጥብ አምጥቶ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከተቀጠረ ሰው የተሻለ ኑሮ አይኖሩም? አንድ ቧንቧ ጠጋኝ ባለሙያ ከፍተኛ ውጤት አምጥቶ ሦስትና አራት ዓመት ሥራ ፍለጋ ከሚኳትን ባለዲግሪ አይሻልም?

ስለዚህ ዕውቀት ማለት የእጅ ወይም የአዕምሮ ሙያ እንጂ የግድ የተሸመደደ የቲዎሪ ትምህርት ስቃይ(ከፍተኛ ነጥብ) መሆን ብቻ አይደለም:: እንዲያውም ሥርዓተ ትምህርታችን ራሱ ይህን ነገር ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት:: የተማሪዎች ትምህርት ተሰጥዖን እና አገር በቀል የሆኑ የዕደ ጥበብ ሥራዎችንም ያካተተ ሊሆን ይገባል:: በዚህ በኩል የኦሮሚያ ክልል ሊመሰገን ይገባል፤ የክህሎት ትምህርት ማሰልጠኛዎች እየተከፈቱ እንደሆነ ሰምተናል::

በአጠቃላይ አንድ ሰው ስኬት ላይ የሚደርሰው በተሸመደደ ዕውቀት ብቻ ሳይሆን በብዙ ተሰጥዖዎች ጭምር ነውና ተማሪዎችን ማሸማቀቅ ይቁም!

# ዓለም አቀፍ

## የቻይናዋ ግዛት ጥንዶች ያለገደብ ልጆች እንዲወልዱ ፈቀደች

በጋዜጣው ሪፖርተር

በቻይናዋ ሴቹዋን ግዛት የሚኖሩ ጥንዶች ያለገደብ ልጆች እንዲወልዱ መፍቀዷን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

የቻይና የሕዝብ ብዛት በ60 ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ መቀነሱ ባለፈው ሳምንት የአገሪቱ መንግሥት አሳውቆ ነበር፡፡ ለአስርተ ዓመታት ሀገሪቷ አንድ ቤተሰብ አንድ ልጅ ብቻ እንዲኖረው የሚያስገድድ ፖሊሲ የነበራት ሲሆን፣ አሁን ግን እንደ አውሮፓውያኑ 2021 ጀምሮ ጥንዶች እስከ ሦስት ልጅ እንዲወልዱ ፈቅዳለች።

አሁን ሴቹዋን ግዛት ባደረገችው የፖሊሲ ለውጥ ያላገቡ ግለሰቦችም ልጆች ወልደው ማሳደግ እንዲችሉ የተፈቀደ ሲሆን ቀደም ብሎ ያላገቡ ሴቶች ልጆቻቸውን ማስመዝገብ አይችሉም ነበር። ቻይና በ1979 የተዋወቀውንና አነጋጋሪ የሆነውን የአንድ ልጅ [ዋን ቻይልድ] ፖሊሲዋን ያነሳችው እንደ አውሮፓውያኑ በ2016 ነበር።

ይህንን ሕግ የጣሱ ወላጆች ቅጣት ይጣልባቸው ነበር። አንዳንድ ጊዜም ሥራቸውን ያጡ ነበር።

በባሕልም ወላጆች ከሴቶች ይልቅ ወንድ ልጅ እንዲኖራቸው ስለሚፈልጉ፣ የአንድ ልጅ ፖሊሲው አስገዳጅ ጽንስ ማቋረጥ እንዲኖርም ምክንያት ሆኗል።

ይሁን እንጂ በ2016 የተደረገው ለውጥ እየቀነሰ የመጣውን የውልደት መጠን አላቆመውም። ባለፈው ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የሞት መጠን ከውልደት መጠን በልጧል።

አሁን ላይ 80 ሚሊዮን ሕዝብ በሚኖርባት እና በአገሪቷ በደቡብ ምዕራብ በምትገኘው ሴቹዋን ግዛት



ነዋሪዎች ያለምንም ገደብ የፈለጉትን ያህል ልጅ መውለድ እንዲችሉ ተፈቅዶላቸዋል። የቻይና ፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ መንግሥት የውልደት መጠንን መጨመር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ ገልጾ ነበር።

መንግሥታቸው እያሽቆለቆለ ያለውን የውልደት መጠን ለመቀልበስ የግብር እፎይታ እና የተሻለ የእናቶች ጤና እንክብካቤ እየሰጠ ነው።

የሴቹዋን የፖሊሲ ለውጥ የተሰማው ቻይና ከኮቪድ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ሞቶች እየታገለች ባለበት ወቅት ነው። አገሪቷ ታኅሣሥ ወር ላይ ዜሮ ኮቪድ ፖሊሲዋን ካነሳች በኋላ ወረርሽኙ በመላ አገሪቷ ተዛምቷል።

ይህ የሕዝብ መጠን መቀነስ ጉዳይ የቻይና ብቻ ሳይሆን ጃፓንን ጨምሮ ሌሎች ጎረቤት አገሮችም ያጋጠማቸው ችግር ነው። የጃፓኑ ጠቅላይ ሚኒስትር በአገሪቷ ያለው የወሊድ መጠን መቀነስ አገሪቱን አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ እንደጣለው በቅርቡ ተናግረዋል።

## እስራኤል እና ፍልስጤም በመካከላቸው ያለውን ውጥረት እንዲያረግቡ አሜሪካ አሳሰበች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ከሰሞኑ ፍልስጤማውያን ባደረሱት ጥቃት ዜጎቼ ተገድለዋል የምትለው እስራኤል ተጨማሪ ወታደሮቿን በዌስት ባንክ ማሠማራቷንና እርምጃ መውሰድ መጀመሯን ተከትሎ በሁለቱ ሀገራት በመካከላቸው የተፈጠረው ውጥረት እንዲያረግቡ አሜሪካ አሳሰበች::

እስራኤል በዚህ ወር ብቻ በዌስት ባንክ በሰነዘረችው ጥቃት 35 ፍልስጤማውያን መገደላቸውንም አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ የሀገሪቱን ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መረጃን ጠቅሶ ዘግቧል::

ሁኔታው ያስጨነቃትና በመካከለኛው ምስራቅ ዲፕሎማሲ ግንባር ቀደም ሚና ያላት አሜሪካም ታዲያ ሀገራቱ ውጥረቱን ከማባበስ እንዲቆጠቡ ጠይቃለች::

የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ከሳዑዲው የቴሌቪዥን ጣቢያ አል ዓረቢያ ጋር በነበራቸው ቆይታ ፤ እስራኤል እና ፍልስጤም በመካከላቸው ያለውን ውጥረት እንዲያረግቡ አሳስበዋል::

በመካከለኛው ምሥራቅ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት በማድረግ ላይ ያሉት ብሊንከን ካይሮ ውስጥ በሰጡት መግለጫ፤ ሁሉም አካላት ነገሩን እንዲያረጋጉ እና ውጥረቱን እንዳያባብሱ መጠንቀቅ አለባቸው ብለዋል::

"ባለፉት ሁለት ቀናት ውስጥ እኛ የምናወግዛቸው እና የምንጸየፋቸው ዘግናኝ የሽብር ጥቃቶች አይተናል” ያሉት ከፍተኛ ዲፕሎማቱ፤ የሁለት መንግሥታት መፍትሔ ለማግኘት መሥራት እንዳለባቸው አጽንዖት ሰጥተዋል::

የዋሽንግተን ከፍተኛ ዲፕሎማት አንቶኒ ብሊንከን ከፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲ እና ከሀገሪቱ



አንቶኒ ብሊንከን

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሳሜህ ሹክሪ ጋር ከተገናኙ በኋላ ግብጽን ለቀው ወደ እስራኤል እና የፍልስጤም ግዛቶች ማምራታቸው ታውቋል::

ብሊንከን በቀጣይ ከእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ እና ከፍልስጤም መሪ ማሕሙድ አባስ ጋር ይነጋገራሉ ተብሎም ይጠበቃል::

በተያያዘ የእስራኤልና እና ፍልስጤም ፍጥጫ እንዲረግብ የሀገራት መሪዎች ጥሪያቸውን ማቅረባቸውን ቀጥለዋል።

የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ሁሉም ወገኖች ከተለመደው “የመጠቃቃት አዙሪት” እንዲወጡ ሲያሳስቡ የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ በበኩላቸው ሁሉም ወገኖች “ከፍተኛ ኃላፊነት” እንዲሰማቸው ጥሪ አቅርበዋል::

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ባለ አስገምጋሚ ድምፁ ጋዜጠኛ - ታደሰ ሙሉነህ

ማህሌት አብዱል



በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ታሪክ ትልቅ አበርክቶ ትተው ካለፉ ሰዎች መካከል ታደሰ ሙሉነህ ዋነኛው ነው:: በሙያው ስርነቀል ለውጥ እንዳመጣ የሚመሰከርለት ይህ ታላቅ ጋዜጠኛ ትውልዱም ሆነ ዕድገቱ እዚሁ አዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ነው:: ታደሰ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በተፈሪ መኮንን የተከታተለ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንና ከፍተኛ ትምህርቱን ደግሞ በልዑል በዕደ-ማርያም ትምህርት ቤት እና በቀድሞው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተከታትሏል:: ጋዜጠኛ ታደሰ በልጅነቱ ጃንሜዳ አካባቢ የሚገኘውን የአንደኛ ክፍለጦር የቲያትርና ሙዚቃ ክፍል ሠራተኞች ወደቤት ሲገቡ እና ሲወጡ በጥንቃቄ ይከታተል ነበር:: በተለይ አርቲስት ጥላሁን ገሠሠን የመሳሰሉትን አንጋፋ አርቲስቶችን በቅርበት ለማየት መታደሉና የበርካታ አርቲስቶች መኖሪያ እሱ ከተወለደበት አቅራቢያ በመሆኑ የተነሳ ልቡ ተዋናይ የመሆን ፍላጎት ሞልቶት ነበር::

ይሁን እንጂ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያዓመትቋንቋተማሪሳለሕይወቱንእስከወዲኛው ሊቀይረው የቻለ ነገር ተፈጠረ:: በአንጋፋው ተዋናይ ተስፋዬ ገሠሠ አማካኝነት የሚመራው የዩኒቨርሲቲው የባሕል ማዕከልን የሚያዘወትረው ታደሰ ሙሉነህ ለኪነ-ጥበብ ይውል ዘንድ ዕድል ተሰጠው፤ የያኔው አፍላ ወጣት ከወጋየሁ ንጋቱ፤ ኃይሌ ገሪማ እና አባተ መኩሪያን ከመሳሰሉት ታላላቅ ሰዎች ጋር መማሩ ከፈጠረለት የደስታ ስሜት ባሻገር የተለየ ነገር አልጠበቀም ነበር:: ሆኖም ያቺ አጋጣሚ ትክክለኛ መክሊቱ ጋዜጠኝነት መሆንዋን አበሰረችለት::

በሙያቸው ምትክ ሊገኝላቸው ከማይችሉ ሰዎች መካከል አንዱ የሆነው ታደሰ ሙሉነህ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በ1960 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሬዲዮ በዜና አንባቢነት የጋዜጠኝነት ሙያን ተቀላቀለ፡፡ በመቀጠልም የቅዳሜ መዝናኛ ፕሮግራምንና በዓይነቱ ልዩ በነበረው የእሁድ ጠዋት ፕሮግራም በማዘጋጀትና በመምራት ለተቋሙም ሆነ ለሙያው እድገት አብዮታዊ ለውጥ አምጥቷል:: በዋናነትም የመጽሔት ፎርማት የመጀመሪያ ፕሮግራም ‹‹እሁድ ጠዋት›› የተሰኘው የመዝናኛ ፕሮግራም እሱን በመላው የሬዲዮ አድማጮች ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ያስተዋወቀው ሲሆን በሙያው የመዝናኛ ጋዜጠኛ አባት የሚል መጠሪያ እስከማግኘት ደርሷል::

ለቀድሞው የኢትዮጵያ ሬዲዮ አድማጮች የሚቆዝሙበትን በርካታ አዳዲስ ፕሮግራሞች ለሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በማስተዋወቅ ስኬታማ መሆን የቻለው እውቁ ጋዜጠኛ ታደሰ ሙሉነህ በሃገሪቱ የሬዲዮ ታሪክ ፋና ወጊ ተብለው የሚታወሱትን ፕሮግራሞች በመቅረፅና በማዘጋጀትም ሙያው አንድ እርምጃ ከፍ በማድረጉ ዛሬም ስሙ ይነሳል:: ለምሳሌ በኢትዮጵያ ሬዲዮ እሁድ መዝናኛና እርሶም ይሞክሩት የተሰኙትን ተወዳጅ የሬዲዮ ፕሮግራሞች ሲወሱና ለዘመናት ሲታወሱ የነበሩ ፕሮግራሞች አዘጋጅና አቅራቢ በመሆን አይረሴ ታሪክ መሥራት መቻሉ ተጠቃሽ ነው::

በባለ አስገምጋሚ ድምፁ ታደሰ ሙሉነህ በተለይም 1973 ዓ.ም በኢትዮጵያ የእሁድ ጠዋቱ የመዝናኛ ዝግጅት ማዘጋጀት ከጀመረ ወዲህ ነበር ስሙ በአየር ላይ መናኘቱን ‹‹የነበረ ይናገር...›› እንደሚባለው ሁሉ በቅርብ የሚያውቁትና የፕሮግራሙ ተከታታዮች የነበሩ የሚመሰክሩለት ሐቅ ነው:: በጊዜው በነበሩ በኢትዮጵያ ሬዲዮ አድማጮች በእለተ ሰንበት ጠዋት በጉጉት ከሚጠበቀው በዚህ ፕሮግራም ብዙዎች ተምረውበታልም፤ ተዝናንተውበታልም:: ለዚያ ዘመን ትውልድ እሁድ ልዩ ትዝታ ነበራት፤ ቀኗ ደርሳ ጠዋት የመዝናኛ ፕሮግራሙን ለመስማት የነበራቸው ጉጉት ዛሬ በሕይወት ያሉት በትዝታ የሚያስታውሱት ሁነት ነው::

አስቀድሞ በነበረው ልማድ መሠረት የኢትዮጵያ ሬዲዮ አቡነ ጴጥሮስ አካባቢ ከሚገኘው ስቱዲዮ በጥንቃቄ የተዘጋጁ ፕሮግራሞችን ሠርቶ ከማሰራጨት በተጨማሪ ሕዝቡን በንቃት ባሳተፈ መልኩ ከስቱዲዮ ውጪ ፕሮግራሞችን የመሥራት ምንም አይነት ልምድ አልነበረውም:: ታደሰ ሙሉነህ የፈጠራ ችሎታውና ለትምህርት ውጭ ሃገር በሄደበት ወቅት ያገኘውን ልምድ በማሰባሰብ አዳዲስ አሠራሮች በማምጣትም የበኩሉን አሻራ ማሳረፍ ችሏል:: በዚያ ጊዜ ሊያውም በተደራጀ መልኩ የሬዲዮ ፕሮግራምን ከስቱዲዮ ለማውጣት በመቻል ሌላ ታሪክ በመሥራቱም ይታወቃል::

**በግል ሕይወቱ ታደሰ የሕዝብን
አድናቆትን እና ክብር ካገኘበት
የኢትዮጵያ ሬዲዮ
ጣቢያ የእንግሊዘኛ ክፍል ባልደረባ ከነበረችው
የሕይወት አጋሩ ጋር
በመጣመር ሕይወቴ ታደሰ ሲል
የሰየማትን ብቸኛ
ሴት ልጁን አግኝቷል**

ታደሰ ሙሉነህ በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ወቅት እንዳለው ‹‹ወቅቱ የቀጥታ ስርጭት ያልተለመደበት ጊዜ ነበር፤ እኔ የማስታውሰው አቶ አሳምነው በቀጥታ ከቤተመንግሥትና የጥምቀት በዓል ጃንሜዳ ሲካሄድ የነበረውን ዝግጅት ተከቼ የገባሁት እኔ ነኝ፤ ያንጊዜ ልጅ ነኝ እሱ ግን ድምፄን ሲሰማ በጣም ነው የገረመው:: ያንጊዜ ደግሞ ማዕረግ ማወቅ አለብህ፤ አለባበስ ማወቅ አለብህ ..... በጣም ጥሩ ጊዜ ነበረን፤ የመማማሪያ ጊዜ ነበረ፤ እኔም ብዙ ነገሮች ለማድረግ ጥሬያለሁ ›› በማለት ስለራሱ ሥራዎች ተናግሯል::

አዳዲስ ነገሮችን ለመሞከር ወደኋላ የማይለው ታደሰ ሙሉነህ አዲስ ሃሳብ ይዞ ብቅ አለ፣ ‹‹እርሶም ይሞክሩት›› የሚል ፕሮግራም ሠርቼ ማቅረብ እንደሚፈልግ ለአለቆቹ ይናገራል:: ፕሮግራሙን በምን አይነት መልኩ እንደሚያቀርብ በአለቆቹ ሲጠየቅ ‹‹በየቀበሌው አዳራሽ እየዞርን፤ በየመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እየገባን አድማጮችን በጥያቄና መልስ በማወዳደር ፕሮግራሙን እናቀርባለን›› የሚለው የታደሰ አጭርና ቀጥተኛ ምላሽ በአለቆቹ ዘንድ ጥርጣሬ ማጫሩ አልቀረም:: አለቆቹ ፍላጎቱን አይተው እንደነገሩ ‹‹ጀምር›› ብለው ፍቃዳቸውን ገለጹለት:: ይሁን እንጂ ፕሮግራሙ ተወዳጅ ስለመሆኑ ሰፊ ጥርጣሬ ነበራቸው:: ሆኖም ፕሮግራሙን በሬዲዮ ማቅረብ ከጀመረ ጊዜ አንስቶ ከፍተኛ ተወዳጅነት በማግኘቱ ለጣቢያው መደመጥ የራሱን ጉልህ ሚና ተጫውቷል:: ፕሮግራሙ ሲጀመር ስኬታማ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ነበር፤ ነገር ግን ፕሮግራሙ በሁሉ ዘንድ ተወዳጅ ሲሆን ከአለቆቹ ምስጋናን አግኝቷል::

የእሁድ መዝናኛ የተለያዩ አዝናኝና አስተማሪ ፕሮግራሞች በስፋት የሚቀርቡበት እንደነበር ይታወሳል:: ምንአልባትም በኢትዮጵያ የሬዲዮ ታሪክ ትልቅ የፕሮግራም አብዮት ማስነሳት የቻለ ነበር ማለት ይቻላል:: የሸገር ሬዲዮ ጣቢያ ባለቤትና የፕሮግራም አዘጋጅ የሆነችው መዓዛ ብሩንና ተፈሪ ዓለሙን የመሳሰሉትን ወጣት ጋዜጠኞችን በመያዝ ዳግሞ አዲስ ነገር ይዞ ብቅ አለ:: ይሄ እያዝናና ቁምነገርን የሚያስጨብጠው ፕሮግራም የተለያዩ ንዑስ ፕሮግራሞችን በውስጡ ያካተተ በመሆኑ የተነሳ አለቆቹ ይህ ፕሮግራም እውን ስለመሆኑ ለእሱ ያልደበቁት ስጋት በውስጣቸው አድሮባቸው ነበር:: ይሁን እንጂ ምስጋና ለእሱ ጥረትና ለመዓዛና ተፈሪ ዓለሙ እንዲሁም ለሌሎቹ ወጣት ጋዜጠኞች ይሁንና የእሁድ መዝናኛ ዘወትር እንደተናፈቀ ዓመታትን በስኬት ማሳለፍ የቻለ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ታላቅ ፕሮግራም መሆኑ ዛሬም ድረስ ይታወሳል ::

የደርግ ዘመን አክትሞ ኢሕአዴግ ሀገሪቱን በተቆጣጠረበት ወቅት ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ በሬዲዮ ጋዜጠኝነት የቆየው ታደሰ ሙሉነህ ጡረታ በመጠየቅ ራሱን ከመንግሥትና ከሚዲያ ሥራ ካገለለ በኋላ የማስታወቂያ ድርጅት በመክፈት በግሉ በመንቀሳቀስ ላይ ነበር:: የታደሰ ሙሉነህ የጋዜጠኝነት ሕይወት ከሞላ ጎደል በስኬት የተሞላ ሲሆን ብዙዎች ከሚያውቁት ከጋዜጠኝነቱ ባለፈ የአዲስ አበባ የዳት ስፖርት ሻምፒዮን ሲሆን ነው:: በሌላ በኩልም ታደሰን በቅርብ የሚያውቁት ጓደኞቹ አንባቢነቱን ይመሰክሩለታል:: በተጨማሪም በሃገሪቱ የሚዲያ ታሪክ ውስጥ ሬዲዮን ለመጀመሪያ ጊዜ ከስቱዲዮ ያወጣ ሁለገብ ጋዜጠኛ ስለመሆኑ ሁሉም አብነት አድርገው የሚጠቅሱት ጉምቱ ጋዜጠኛ ነው:: በተለይም በወቅቱ አንድ ለእናቱ ለነበረው የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ የአድማጮቹን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር በማድረግ ሌላ ደማቅ ታሪክ በመፃፉም ለሃገር የማይዘነጋ ውለታን አሳርፎ ያለፈ ሰው ነው::

ሁለገቡ ጋዜጠኛ የአዳዲስ ሃሳብ አመንጪ፤ የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ ታደሰ ሙሉነህ ከዜና አንባቢነት እስከ ዋና ክፍል ኃላፊነት በሬዲዮ ጣቢያ ያገለገለ ሲሆን አዲስ ቻምበር ድምጽ መሥራችና የፕሮግራም መሪ በመሆን አገልግሏል:: ለሰባት ዓመታትም የሞሐ ሳምንታዊ ፕሮግራሞችን እንዲሁም ደግሞ ‹‹እሁድን እንደገና›› በተሰኙት ፕሮግራሞች በሸገር ኤፍ ኤም ያቀርብ ነበር:: ብዙዎች የማያውቁትና የሚገርመው ነገር ግን ታደሰ የሬዲዮ ብቻ ሳይሆን የቴሌቪዥን ስፖርት ጋዜጠኛ ሆኖ ጭምር መሥራቱን ነው:: ከዚህ ባሻገር በሞሐ ሕዝብ ግንኙነት ውስጥም የሠራው ታደሰ በጡረታ ዘመኑ ሳይቀር በርካታ ሥራዎችን አበርክቷል:: ይህን አንጋፋ ጋዜጠኛ ለትውልድ ተሻጋሪ የሆኑ ሥራዎችን ከማበርከት ባለፈ እንደመዓዛ ብሩና ተፈሪ ዓለሙን የመሰሉ ብርቱና ምርጥ ጋዜጠኞችን በማፍራትም ያበረከተው አስተዋፅኦ የማይዘነጋ ነው::

በግል ሕይወቱ ታደሰ የሕዝብን አድናቆትን እና ክብር ካገኘበት የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ የእንግሊዘኛ ክፍል ባልደረባ ከነበረችው የሕይወት አጋሩ ጋር በመጣመር ሕይወቴ ታደሰ ሲል የሰየማትን ብቸኛ ሴት ልጁን አግኝቷል:: በቤተሰቡም ደስተኛ የነበረ ሲሆን በግሉ ድጋፍ የሚያደርግላቸው ሦስት አይነስውራን ወጣቶችም በዲግሪ ተመርቀውለታል:: ከአስር በላይ በሚሆኑት ሃገራት ያሰባሰበውን እውቀት ለአዲሱ ትውልድ በማካፈሉ ቤቱ ይቁጠራቸው የሚባሉ በርካታ የሙያ ልጆችንም አፍርቷል:: ታደሰ አንድ ወቅት ላይ ‹‹የተቻለኝን የሙያው ባለቤት እንዲሆኑ ጥረት አድርጌያለሁ:: አሁን የምትሰሚቸው ልጆች ሁሉ ጥሩ ቦታ ደርሰው ሳያቸው የሚሰማኝ የመንፈስ ደስታ ትልቅ ነው›› ሲልም ተናግሯል::

ጋዜጠኛ ታደሰ ጡረታ ከወጣም በኋላ ከሙያው ሳይለይ በርካታ ሥራዎችን በመሥራቱ ከፍተኛ እውቅና ከተለያዩ አካላት ተሰጥቶታል:: በሙያው ካገኛቸው በርካታ ሽልማቶች መካከልም ከኢትዮጵያ የሥነ- ጥበባትና መገናኛ ብዙኃን ሽልማት ድርጅት ያገኘው በዋናነት ይጠቀሳል::

ታላቁ ጋዜጠኛ ታደሰ ሙሉነህ ከአራት አስርተ- ዓመታት በላይ ከዜና አንባቢነት ጀምሮ በፕሮግራም አዘጋጅነት፣ በፕሮዳክሽን ኃላፊነት፣ በዋና ክፍል ኃላፊነትና በተጠባባቂ የመምሪያ ኃላፊነት የኢትዮጵያ ሬዲዮ ላይ ብቻ ፕሮግራሞች አዘጋጅና አቅራቢ በመሆን ጡረታ እስከወጣበት ጥቅምት 1986 ዓ.ም ድረስ ለ26 ዓመታት አገልግሏል:: ከጡረታ በኋላም ለሕይወቱ ማለፍ ምክንያት የሆነው ሕመም እስካደናቀፈው ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይይል ለሙያው እድገት ዋጋ ከፍሏል:: ጋዜጠኛ ታደሰ ባደረበት ሕመም በአዲስ አበባ፣ በጆሐንስበርግ (ደቡብ አፍሪካ) እና ባንኮክ (ታይላንድ) ሕክምናውን ሲከታተል ቆይቶ በ66 ዓመት ዕድሜው ከሚወደው ሙያና ሕዝብ በሞት ተለይቷል:: ይሁንና በሙያው ውስጥ ላሉ የዘርፉ ተዋናዮችም ሆነ ለሃገር ትቶት ያለፈው አሻራ ዛሬም ደማቅ ሆኖ እያበራ ይኖራል::

# ስፖርት





## አሰልጣኝ ውበቱ አባተ በቻን ለተመዘገበው ውጤት ይቅርታ ጠየቁ

ብርሃን ፈይሳ

በአልጄሪያ አስተናጋጅነት እየተካሄደ በሚገኘው 7ኛው የአፍሪካ ሻምፒዮን ሺፕ (ቻን) ተሳታፊ ከሆኑ ቡድኖች መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን መሆኑ ይታወሳል:: በምድብ አንድ የተደለደሉት ዋልያዎቹ አንድ ነጥብ አስመዝግበው ከምድቡ የመጨረሻውን ደረጃ በመያዝ በጊዜ ተሰናብተዋል። ይህንንም ተከትሎ የዋሊያዎቹ አሰልጣኝ ውበቱ አባተ ከትናንት በስቲያ በሰጡት መግለጫ የስፖርት ቤተሰቡን ይቅርታ ጠይቀዋል::

በፌዴሬሽኑ ዋና ፀሐፊ አቶ ባሕሩ ጥላሁን እና በዋልያዎቹ አሰልጣኝ ውበቱ አባተ መግለጫው ሲሰጥ የዋልያዎቹ አለቃ ባቀረቡት ማብራሪያ ላይ በተመዘገበው ውጤት ማዘናቸውን እና ለዚህም ኃላፊነቱን በመውሰድ ይቅርታ እንደሚጠይቁ በይፋ ተናግረዋል።

በሃገር ውስጥ ሊጎች ብቻ የሚጫወቱ ተጫዋቾች የሚካፈሉበት ይህ ውድድር እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገራት ዋናውን ቡድናቸውን ይዘው ስለሚካፈሉ ለውጤታማነት የተሻለ ዕድል እንደሚኖራቸው ተጠብቆ ነበር። ይሁን እንጂ ብሔራዊ ቡድኑ በርካታ ተጫዋቾቹን በጉዳት ምክንያት ሳያካትት እና ከ10 በላይ የሚሆኑ ወጣት ተጫዋቾችን በመያዝ ነበር ወደ አልጀርስ ያመራው:: በመጀመሪያዎቹ ሁለት የምድብ ጨዋታዎች ላይ መልካም እንቅስቃሴ በማሳየቱ በሊቢያው ጨዋታ ሶስት ነጥብ ለማስመዝገብ ነበር ወደ ሜዳ የገባው:: ይሁንና በጥቃቅን ጉድለቶች ሽንፈትን አስተናግዷል፤ ለዚህም ሙሉ ኃላፊነቱን እንደሚወስዱ ነው አሰልጣኙ የገለጹት:: የተጠበቀው ውጤት ባለመገኘቱም የስፖርት ቤተሰቡን ይቅርታ ጠይቀዋል::

ቡድን መገንባት ቀላል ሥራ ባይሆንም ተጠባቂ ቡድን



አሰልጣኝ ውበቱ አባተ፣

መገንባታቸውን የጠቆሙት አሰልጣኙ፤ የግብ ዕድል በመፍጠር ረገድም ቡድኑ እየተሻሻለ መምጣቱንም ነው ያስገነዘቡት:: አሰልጣኙ እንዳብራሩት፣ በርካታ ወጣት ተጫዋቾች የውድድር ዕድል ባገኙበት በዚህ ውድድር ላይ የተሳተፈው ቡድን በአጭር ጊዜ የተገነባ ቢሆንም ከፍተኛ ተነሳሽነት ነበረው:: ስለዚህ የቡድኑን አባላት መንቀፍና ሞራላቸውን መንካት ተገቢ እንዳልሆነ ተናግረዋል።፡ ቡድኑን ወደ መምራት ከመጡ በኋላ በሃገራቸው አራት ጨዋታዎችን ብቻ ማድረጋቸውን ያስታወሱት አሰልጣኙ፤ የተቀሩትን ጨዋታዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ስታዲየሞች አለመኖር ምክንያት ከሃገር ውጪ በማከናወን ላይ ይገኛሉ:: በመሆኑም ይህም ለውጥ መሆኑን በማመን ቡድኑን ቢያበረታና በቅርቡ በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ከጊኒ ጋር ለሚያደርገው ጨዋታም ሕዝቡ ከጎኑ ቢቆም መልካም መሆኑንም አመላክተዋል::

ዋና ፀሐፊው አቶ ባሕሩ ከውድድሩ ጋር በተገናኘ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ እንደገለጹት፣ ብሔራዊ ቡድኑ ወደ ሞሮኮ ለዝግጅት ተጉዞ ሁለት የልምምድ ጨዋታዎችን ያደረገው በአልጄሪያ ያለው ወቅታዊ የአየር ሁኔታ ተጠንቶ ነው። ብሔራዊ ቡድኑ በውድድሩ ከምድብ ይወድቃል በሚል ጨለምተኛ ምክንያት ወደ ሀገር ቤት መመለሻው ትኬት በጊዜ አለመቆረጡን ጠቅሰውም ቡድኑ ከምድብ ከወደቀ በኋላ ግን የአውሮፕላን ትኬት ለማግኘት እንዳልተቻለ ጠቁመዋል። በዚህም ልዑካን ቡድኑን በአስገዳጅ ሁኔታ በሦስት ዙር ወደ አገሩ ለመመለስ መገደዱን አመላክተዋል።

አቶ ባሕሩ አክለውም፣ ብሔራዊ ቡድኑ በውድድሩ ወቅት የመለያ እጥረት አጋጥሞት ነበር የተባለው ጉዳይ “ብሔራዊ ቡድኑ ከሞሮኮ ተነስቶ ወደ አልጀርስ ሲሄድ የትራንዚት ቆይታ ስለነበረው ሻንጣዎች ካዛብላንካ ላይ ነው የተጫኑት ፤ ሻንጣዎቹ የሚጠበቁት ደግሞ አልጀርስ ነው። በዚህ ሂደት የአራት ተጫዋቾች ሻንጣ እና ቡድኑ ከያዘው ቁሳቁስ መካከል አንድ ሻንጣ በትራንዚት ምክንያት አልመጣም። ይሄ ተለዋጭ ማሊያ ነው። እንደተወራው ፌዴሬሽኑ ያላዋቂዎች እና የሰነፎች ጥርቅም አይደለም። ቢያንስ ምክንያታዊ ሆነን ብንነጋገር ጥሩ ነበር። ይህ የተፈጠረው በትራንዚት ምክንያት ነው። ግን ቡድኑ ማሊያውን አርጎ ሲጫወት ነበር።” ብለዋል። አቶ ባሕሩ አያይዘው በተመዘገበው ውጤት እንደ እግር ኳስ ፌዴሬሽን እንዳዘኑ አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ በዚህ የውድድር መድረክ ላይ ዘንድሮ ለሦስተኛ ጊዜ ተካፋይ መሆኗ ይታወቃል:: ይሁንና ተሳትፎዎቿ ከምድብ ያለፉ በውጤትም የታጀቡ ሊሆኑ አልቻሉም:: በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው በዚህ ውድድር ላይም ዋልያዎቹ ከዚህ ቀደም ከተመዘገበው የተሻለ ውጤት የማስመዝገብ ኃላፊነት ተጥሎባቸው ነበር። ለዚህም ሲባል በሃገር ውስጥ እንዲሁም የውድድሩ አዘጋጅ ከሆነችው አልጄሪያ ጋር ተቀራራቢ የአየር ሁኔታ ባላት ሞሮኮ ዝግጅት ተደርጓል። ቡድኑ በሰሜን አፍሪካዊቷ አገር በነበረው የልምምድ ቆይታ ከሞሮኮ ከ23 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ጋር ሁለት የአቋም መለኪያ ጨዋታዎችን አከናውኗል። ይሁን እንጂ በውድድሩ ባከናወናቸው ጨዋታዎች ከሞዛምቢክ ጋር ያለ ግብ በመለያየት እንዲሁም በአልጄሪያ እና ሊቢያ ተሸንፎ አንድ ግብ እና አንድ ነጥብ ብቻ በማስመዝገብ በጊዜ ወደ ሃገሩ ለመመለስ ተገዷል::


## ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ

የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ከዚህ በታች በተጠቀሰው ክፍት የሥራ መደብ ላይ ቋሚ ሠራተኞችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት | ተፈላጊ ችሎታና መመዘኛ መስፈርት | ደረጃ | ብዛት | ደመወዝ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሲኒየር ሴክሬታሪ | በሴክሬታሪያል ሳይንስ በቢሮ አስተዳደር ኮሌጅ ዲፕሎማ /ዲግሪ እና 3/1 ዓመት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ያለው/ላት | 10 | 2 | በስምምነት |
| 2 | የቀላል መኪና ሾፌር | 8ኛ/10ኛ/12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች እና 3ኛ መንጃ ፈቃድ ያለው/ላት 4 ዓመት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ያለው/ላት | 7 | 1 | በስምምነት |


**ማሳሰቢያ**፡- ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የተፈላጊ ችሎታ መስፈርት የምታሟሉ አመልካቾች ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ማስረጃችሁን በመያዝ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቢሮ ቁጥር 53 እየቀረባችሁ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

አድራሻ፡- ከመገናኛ ወደ ጉርድ ሾላ በሚወስደው መንገድ ላይ ሆሊ ሲቲ ሴንተር አጠገብ ወይም ከFAO መ/ቤት ጎን፡፡

ስልክ ቁጥር፡- 011-6 46 09 61, 011 646 0386


**የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት**

መሠረት ማኒፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግ/ ማኅበር
MESERET MANUFACTURING



ቆርቆሮዎችን በተለያየ ቀለም ያገኛሉ!
0923 39 4308/0923 30 4566/0113811017

0.40MM 28



የበረንዳ ቤት
ጣራ ታይልስ
መደበኛ ጣራ ቆርቆሮ
ኤጋ:300,400,500
CORRUGATED
GREEN,RED,BLUE



0923 39 4308/0923 304566/0113811017